# ዓባይ

ዓባይ 9ኛ; ዓመት ቁጥር 6 መጋቢት; 2015 ዓ/ም

www.bdu.edu.et

## የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከሰላም ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ያሰለጠናቸውን በጎፈቃደኛ ወጣቶች አስመረቀ



የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከሰላም ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ያሰለጠናቸውን በጎፈቃደኛ ወጣቶች አስመረቀ::

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከሰላም ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ያሰለጠናቸውን ከ1600 በላይ 6ኛ ዙር የበጎ ፈቃድ ብሔራዊ አገልግሎት ሰልጣኞችን የዩኒቨርሲቲውን ከፍተኛ አመራሮች ጨምሮ የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ እና የክልል ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት በአብክመ ስራ አመራር ማሰልጠኛ ተቋም አዳራሽ አስመርቋል።

በምረቃ ስነ ስርዓቱ ላይ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአስተዳደር ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት አቶ ብርሃኑ ገድፍ ባደረጉት ንግግር የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍል በመምጣት ስልጠናውን ወስደው ለዛሬው የምረቃ ቀን ለደረሱ ሰልጣኝ ተመራቂዎች የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት አስተላልፈው፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ እኛ ልጆቿ መልካም ስራ እንድንሰራላት እና አሁን ካለችበት ምስቅልቅል የሰላም እጦት ውስጥ ወጥታ ወደ ተስተካከለ የሰላም መስመር እንድትገባ ሁላችንም የድርሻችንን እንወጣ ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከምረቃ በኂላ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት በምትመደቡበት አካባቢ በስልጠና ወቅት ያገኛችሁትን እውቀት፣ ጉልበት እና ሙሉ አቅማችሁን በመጠቀም ሕዝብን ከሕዝብ የሚያቀራርብ እና አንድ የሚያደርጉ በጎ ስራዎችን መስራት እንዳለባቸው አሳስበው ተመራቂዎችም የተሰጡትን እድል በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ ለተመራቂ ወጣቶች የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህይወት ዘመን አምባሳደሮች መሆናቸውን አብስረዋል።

በምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የተገኙት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር ስዩም መስፍን በበኩላቸው የሰላም ሚንስቴር ከተቋቋመባቸው መሰረታዊ ሀላፊነቶች ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው በሀገራችን ዘላቂ ሰላም የሚሰፍንበትን መሰራታዊ መንገዶችን ማመቻቸት መሆኑን ጠቅሰው በአገሪቱ የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶችና የኢትዮጵያን ብዘሃ ባህሎችና እሴቶች አውቀው የሚያሳውቁ ወጣቶችንከተለያዩየአገሪቱአካባቢዎችበመመልመል እና በማሰልጠን ማሰማራቱን ገልፀዋል።

ወደ ገጽ 13 የዞረ

### በውስጥ ገፆች

ርዕሰ አንቀጽ--- ------------------------------ገጽ3

አንዱ ክፍል ወግ ------------------------ገጽ 6

የፔዳጎጂና ትምህርት ምርምር ተቋም-----ገጽ 8

ባሕር ዳር ሀይል (Energy) ማዕከል---------ገጽ 11

STEM INCUBATION CENTER)------- --ገጽ 12

ዶ/ር ፈነታነሽ ኃይሌ ጋር የተደረገ ቆይታ--ገጽ 14

# ዓባይ

በ2006ዓ/ም ተመሰረተ።

ዓባይ በኢንፎርሜሽን ስትራቴጂክ ኮሚዩኒኬሽን ም/ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት እየተዘጋጀ
የሚታተም ወርሃዊ ጋዜጣ፤

ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ!

**ዋና አዘጋጅ**
ግርማው አሸብር
girmawashebir@gmail.com

**ም/ዋና አዘጋጅ**
አለባቸው አለሙ
aalemu45@gmail.com

**ፎቶ ግራፍ**
ታምራት አታላይ
በሪሁን ታረቀኝ
ቤተልሄም ወርቅነህ
አገሬ ዘለቀ

**ስርጭት**
አልማዝ አምበሉ
ኑኑሽት ምትኩ
ትርንጎ ወለላው
ወርቅነሽ አበባው
ቀራለም አድማሱ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
አለባቸው አለሙ
ቤተልሄም ወርቅነህ
አገሬ ዘለቀ

**ፀሀፊ**
አበባ ካሳው
መልሰው አደመ

**አድራሻ፡-** ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ
ባሕር ዳር ጥበብ ህንፃ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 512
ፖ.ሳ.ቁ 79
ስ.ቁ +251 58 3206059

**ሾፌር**
ፈንታሁን አንሙት

**ዘገባ**
ወንዳለ ድረስ
ሙሉጌታ ዘለቀ
ሙሉጎጃም አንዱዓለም
ሽጋው መስፍን
ባንቹ ታረቀኝ

ዓባይ ህትመትና የወረቀት ፓኬጅንግ ፋብሪካ ታተመ መጋቢት 2015ዓ/ም


Motto:

Wisdom at the source of the Blue Nile

Vision:

BDU aspires to be of the leading research —intensive Universities in Africa and the first choice in Ethiopia by 2030.

Mission;

Promote advanced research and innovation on the basis of the country's requirements;
Produce graduates with relevant professions and necessary competences (knowledge, skills and attitude ) to respond to the national labor market requirement to eventually ascertain the global competitiveness of the country;
Improve lives through evidence-based and transformative community engagement;
Enhance demand-driven and problem solving technology transfer.



Abbay 9th year, No, 6 March 2023

# ርዕሰ-አንቀጽ

## «የኢትዮጵያ ጥንታዊ ጀግኖች አርበኞች የድል ቀን ሲታወስ»

የኢትዮጵያ ጥንታዊ ጀግኖች አርበኞች የድል ቀን ጀግኖች አርበኞች የብሔር፣ የቀለምና የሐይማኖት ልዩነት ሳይገድባቸው፣ በፅኑ የሀገር ፍቅር ስሜት እና በአልበገር ባይነት ቆራጥ ተጋድሎ ሀገራችን ኢትዮጵያን ከውጭ ወራሪ ኃይል በነፃነት ጠብቀው ለአሁኑ ትውልድ ያቆዩበት አንፀባራቂ ገደል ሚዘከርበት ታሪካዊ ቀን ነው፡፡

በቀደሙት ጀግኖች ኢትዮጵያን አኩሪ ተጋድሎ ታፍራና ተከብራ የኖረችው የዛሬዋ ኢትዮጵያ ከውስጥና ከውጭ በተሰለፉባት እኩይ ኃይሎች የተናበበ የጥፋት ሴራ አያሌ ፈተናዎች የተጋረጠባት ሲሆን፣ በአንፃሩ ደግሞ እንደቀደምት አያት፣ ቅድመ-አያቶቻቸው ሁሉ የኢትዮጵያውያንን አንድነትና አብሮነት በማጠናከር መላው ህዝቦቿን ወደ ከፍታው ማማ የማድረስ ብሩህ ተስፋ የሰነቁ አርቆ አሳቢ ብልህ ልጆቿ ይህን የፈተና ጊዜ በጥበብ በማለፍ ትንሣኤዋን እውን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች፤ ለሃገር ነጻነት፣ አንድነትና ክብር በጋራ በመቆም፤ የኢጣልያ ፋሽስት ወራሪ ሃይልን በመመከት፤ ከሁሉም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች በመጉረፍ ጠላትን ያስጨነቀበት እና ድል ያደረገበት አልበገር ባይነትን ያስመሰከሩበት «የኢትዮጵያ ጥንታዊ ጀግኖች አርበኞች የድል ቀን መታሰብያ» በየአመቱ ሚያዝያ 27 ቀን ይከበራል፡፡

በ1888 ዓ.ም. በአድዋ በኢትዮጵያውያን ጀግኖች ድል የተደረገችው ፋሺስት ኢጣሊያ ሽንፈቱን ለመበቀል በማሰብ ከ40 ዓመታት በኋላ አዲስ የወረራ ስልት በመቀየስ በ1928 ዓ/ም ኢትዮጵያን ብትወርም ኢትዮጵያውያን ጀግኖች አርበኞች እስከ 1933 ዓ/ም ወራሪውን ኃይል ለ5 ዓመታት በፅናት ታግለዋል፡፡ ፋሺስት ኢጣሊያን ኢትዮጵያን ዳግም ቢወርም ጀግኖች ዐርበኞች ኢትዮጵያውያን በዱር በገደሉ እየተዋደቁ ረፍት ነስተው አገራቸውን ሳያስደፍሩ ነጻነቷን ጠብቀው አቆይተዋል፡፡

ጥንታዊ ጀግኖች አርበኞች የጣልያንን ጦር አምስት ዓመት ተጋድለዉ የሃገር ነፃነትን ማስከበራቸዉ፤ አኩሪ ድል የመቀዳጀታቸዉን ታሪክ ህያዉ አድርጎ ለማቆየት ብዙ መስዕዋትነት ከፍለዋል፤ የአሁኑ ትዉልድም የሀገሩን ነጻነትና ክብር ለመጠበቅ ብዙ ስራዎችን መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ከአባቶች የወረስነውን የአገር ፍቅር እና አንድነት ዛሬ ሰላም ልንገነባበት ይገባል፡፡ ለጀግኖች አርበኞች የሚገባቸውን ክብር በመስጠት የጀግኖች አባቶች አገር ወዳድነት እና ኅብረት ለዛሬው ትውልድ ትምህርት ሆኖ መተላለፍ ይገባዋል፡፡

የነገዋን ኢትዮጵያ ብሩህና ለዜጎቿ ምቹ በማድረግ ረገድ የዛሬ ልጆቿ የማይናቅ ሚና አለን፡፡ ሀገራችን ከገጠማት ፈተና ተሻግራ ወደ ምንመኝላት የከፍታ ማማ ላይ ትወጣ ዘንድ እንደ ግለሰብም ይሁን እንደ ማህበረሰብ ሁላችንም ማበርከት የምንችለው ብዙ የአርበኝነት ተግባር አለ፡፡ በቅድሚያ ሠላማችንን በአስተማማኝ መልኩ ማረጋገጥ፣ ብሔራዊ መግባባትን ማጠንከር እና የጋራ ሀገራችንን በህብረት መገንባት ይገባል፡፡

መልካም የአረበኞች ቀን!

## የ2015 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ተፈታኝ ተማሪዎች የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን ጎበኙ

በባንቹ ታረቀኝ




የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ 60ኛ ዓመት የምስረታ በዓል አውደ ርዕይ ኮሚቴ ከባሕር ዳር ከተማ ከካቶሊክ ፣ከኤስኦኤስ እንዲሁም ከሰቲም/ STEM/ ትምህርት ቤቶች የመጡ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የዩኒቨርቲውን የተለያዩ ግቢዎች አስጎበኘ፡፡

ጉብኝቱን በእንኳን ደህና መጣችሁ የከፈቱት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ክፍል የሳይኮሎጂ መምህር አቶ ታምሩ ደለለኝ ስለ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከአመሰራረቱ ጀምሮ አሁን እስካበት ደረጃ ያለውን የ60 ዓመት ጉዞ ታሪክ እና ያሳለፋቸውን ሁነቶች እንዲሁም በዚህ ዩኒቨርሲቲ ተምረው ትላልቅ ደረጃ ስለደረሱ፣ በአመራር ላይ ስላሉ ግለሰቦች፣ ስለ ትምህርት አሰጣጥ ጥራቱ ለተማሪዎች ገለጻ አድርገዋል፡፡

በመቀጠልም የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአውደ ርዕዩ ዝግጅት ኮሚቴ አባል ወ/ሮ ኤልዳና ደሳለኝ የዚህ ጉብኝት ዓላማ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ60ኛ ዓመት ጉዞው ውስጥ ምን እንዳደረገ እና የት እንደደረሰ ለማስተዋወቅ በተጨማሪም እኒህ የሚጎበኙ ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲውን ምንነት አውቀው ለወደፊቱ ተመራጭ እንዲያደርጉት፣ ስለዩኒቨርሲቲ ያላቸው ንቃተ ህሊናም ከፍ እንዲል ለማድረግ ነው ብለዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ወ/ሮ ኤልዳና ወደ ፊት በባህር ዳር ከተማ ስር ያሉ ሌሎች የመንግስት ተማሪዎችም በዚህ ጉብኝት እንደሚሳተፉ እና ፕሮግራሙም እስከ ሰኔ 2015 ዓ.ም እንደሚቆይም ገልጸዋል፡፡ ከትምህርት ቤቶች የመጡ ተማሪዎች ስለጉብኝቱ ከሰጡት ሀሳብ መካከል ከሰቲም/ STEM/ ማበልጸጊያ ማዕከል የመጣው ተማሪ ዮናታን አባይነህ ጉብኝቱ ጥሩ እንደሆነ እና የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የ60ኛ ዓመት ተመልክቶ ታሪኮችን ሰምተናል፡፡ የሰማነው ታሪክ ደስ የሚል ነበር፤ እኛም በዚህ ዩኒቨርሲቲ ገብተን እንዲህ ያለ ታሪክ እንደሚኖረን ተስፋ አደርጋለሁ ብሏል፡፡

ተማሪ ዮናታን አክሎም የተለያዩ ነገሮችንም አይተናል ይህን እድል ያላገኙት ሌሎች ተማሪዎችም እንዲጎበኙ ዩኒቨርሲቲው ቢያመቻችላቸው ሲል ሀሳቡን ገልጿል፡፡ ከኤስኦኤስ/SOS/ ትምህርት ቤት የመጣችው ተማሪ እና ያረጋል ጉብኝቱ አስደሳች እንደሆነና ሌሎች ተማሪዎችም እድሉ ቢመቻችላቸው እና በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ወደፊት የመማር እድሉ ቢገጥመኝ ደስተኛ ነኝ ብላለች፡፡

ሌላዋ ተማሪ ከካቶሊክ ትምህርት ቤት የመጣችው ናርዶስ ኃይሌ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ 60ኛ ዓመቱን አስቦ እኛን በመጥራቱ ደስተኛ ነን፡፡ ምክንያቱም የብዙዎቻችንን ህይወት እዚህ ዩኒቨርሲቲ ላይ በመመስረቱና ብዙ ነገሮችን ማየት በመቻላችን ደስተኛ ነን ከዚህ በፊት እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎችን አይተን አናውቅም እናም ይህን እድል በማግኘታችን እናመሰግናለን፤ ትምህርት ቤቱ ወደ ፊትም እንዲህ አይነት ጉብኝቶችን ቢያዘጋጅ ጥሩ ነው ለተማሪዎች መነሳሳትን ይፈጥራል ብላለች፡፡

**ሠሞነኛ** ይህ አምድ ከዜናዎች በተጨማሪ ወቅታዊ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ሀተታዊ ጽሁፎች ይቀርብበታል

## የመሬት አስተዳደር ኢንስቲትዩት ሲያሰለጥናቸው ለነበሩ ሠልጣኞች የማጠቃለያ መርሐግብር አካሄደ





የመሬት አስተዳደር ኢንስቲትዩት ከየካቲት 19 ጀምሮ እስከ መጋቢት 24/2015ዓ/ም ሲያሰለጥናቸው የነበሩ ሠልጣኞች የማጠቃለያ መርሐግብር በጥበብ አዳራሽ አካሄደ። ተስፋዬ ሽፈራው( ዶ/ር) የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ለሠልጣኞችና ለእንግዶች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ተስፋዬ(ዶ/ር ) ሰልጣኞች ዩኒቨርስቲው የ60ኛ ዓመት የአልማዝ ኢዮቤልዩ በዓል በሚያከብርበት ወቅት ልዩ ስልጠናበማግኘታችሁእናንተም የ60ኛ ዓመት በዓላችን አካል በመሆናችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋል።

ተስፋዬ(ዶ/ር ) አክለውም ለአገራችን የመልካም አስተዳደር ችግር መንስኤ፣ የሁሉም ዜጎች ችግርና በተለይ ደግሞ የከተማ መሬት አስተዳደር ላይ እንደዩኒቨርሲቲ የመፍትሄ አካል ለመሆን በከፍተኛ ትኩረት የተሠጠው የመሬት አስተዳደር ኢንስቲትዩት ሰፊ አገራዊ ድርሻ ወስዶ እየሰራ ስለመሆኑ አስገንዝበዋል።

የመሬት አስተዳደር፣ የዘመነ የከተሞች ፕላን እና አጠቃቀም ላይ የሠለጠኑ ዜጎችን ከማፍራት ጎን ለጎን ይሄን መሠል የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት ሰፊ ልምድ እንዳለውና ይሄን በመገንዘብ የኢፌዲሪ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የገቢዎች ሪፎርም ፕሮጀክት ስልጠናውን እንድንሰጥ ስለመረጠንም እጅግ አክብሮት አለን ብለዋል።

በቀጣይም ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በትብብር ለመስራት የነበረውን ግንኙነት አጠናክሮ ለመቀጠል ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፍላጎት እንዳለው ም/ፕሬዚደንቱ ተናግረዋል።

የኢፌድሪ ከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ዴታ የሆኑት ክቡር አቶ ፈንታ ደጀን የመዝጊያ መርሐግብሩ ላይ በመገኘት ለሠልጣኞች መልዕክት አስተላልፈዋል። ዩኒቨርስቲው ስልጠናውን በመስጠት ለነበረው ተሳትፎ እና የትብብር ስራ ያላቸውን አድናቆት ገልጸው በዘርፉ ባለሙያዎችን ለማፍራት በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም እየተሠጠ እና ከ5ሺህ በላይ ባለሙያዎችን በአገር አቀፍ ደረጃ ለማፍራት ተጠናክሮ የሚቀጥል ስለመሆኑ ተናግረዋል።

በመጨረሻም ለስልጠናው መሳካት አስተዋጽኦ ላደረጉ ለአብክመ ከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ፣ ለባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ እና ለአብክመ የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ምስጋና አቅርበዋል።

## ከዶክተር እሸቱ ጌታሁን ጋር---ከገጽ 11 የዞረ





አባይ፡- ይህ ማዕከል ያስመዘገበው ስኬት ምንድን ነው?

ዶ/ር እሸቱ፡- ይህ ማዕከል ያስመዘገበው ስኬት ማዕከሉ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ጠንካራ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል። በትምህርት ዘርፉ ከ 176 በላይ በሁለተኛ ድግሪ ከ 4 በላይ የሶስተኛ ድግሪ ተማሪዎችን እስካሁን ድረስ አስመርቋል።በምርምር በኩልም ብዙ ስራዎችን የሰራ ሲሆን ከ 58 በላይ የምርመር ህትመቶችን በአለም አቀፍ አሳታሚ ድርጅቶች አሳትሟል። የተለያዩ የትምህርት ውይይቶችንም በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች አካሂዷል፣ከ 150 በላይ ትምህርት ነክ ውይይቶች ተከናዉነዋል።የተለያዩ ሀገር አቀፋዊ እና አለም አቀፋዊ ኮንፈረንሶች ተከናዉነዋል።ከ 3 በላይ አለም አቀፍ የምርምር ፕሮጀክቶችን በማሸንፍ በኢነርጂው ዘርፍ ሰፋ ያሉ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል። በቴክኖሎጂ ሽግግርና በማህበርሰብ አገልግሎትም በርካታ ስራዎችን የሰራ ሲሆን በአሁኑ ሰአትም ከተለያዩ አለም አቀፍ አጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን ችግር ፈች የሆኑ የማህበረሰብ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል።ከነዚህ ዉስጥ በዳንግላ ወረዳ በዳንግሽታ ቀበሌ እያከናወነ ያለው የጸሀይ ሀይልን በመጠቀም የከርሰምድርን ዉሃ በማዉጣት ለአካባቢው ማህበረሰብ ለመስኖ ስራና ለመጠጥ ዉሃ አገልግሎት ጥቅም ላይ እያዋለ ይገኛል።

ምስል 1፣ሶላር እነርጂን በመጠቀም የመስኖ ስራ በስንዴ ሰብል ልማት ላይ (በዳንግሽታ ቀበሌ) በዚሁ ቀበሌ በገጠር ያሉ ወጣቶችም ከፀሃይ ሀይል የሚመነጨዉን ኤለክትሪሲቲ በመጠቀም የተለያዩ የእርሻና የንግድ እንቅስቃሴዎችን በመስራት ላይ ይገኛሉ።

- ሶላር ኢነርጂን በመጠቀም ወደ 8 ሄክታር መሬት በመስኖ ሰብል ልማት ለምቷል (በስንዴ እና በድንች ሰብል ልማት)
- ከ30 በላይ አርሶ አደሮችም በመስኖ ሰብል ልማት ተሳታፊና ተጥቃሚ ሁነዋል
- በወተት ማቀዝቀዥያ እና በጣዉላ መሰንጠቂያ ስራ ላይ ስራ ፈጣሪዎችን በማደራጀት እና ወደስራ ለማስገባት የተለያዩ የመሰረተ ልማት ሰራዎች ተከናዉነዋል።
- በመጠጥ ዉሃ ከ 1800 በላይ የሚሆኑ አርሶ አደሮች እና ቤተሰቦቻቸው ተጠቃሚ ሁነዋል።

ባጠቃላይ ከ 15 በላይ የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን ለተለያዮ የህብረተሰብ ክፍሎች አድርሷል። በአሁኑ ሰአትም በመማር ማስተማሩ እና በምርምር ስራዎች ላይ ጠንካራ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል።

አባይ፡- እነዚህን አሁን የተነሱትን ስራዎችበምትሰሩበትጊዜያጋጠሟችሁ ተግዳሮቶችስ ይኖሩ ይሆን?

ዶ/ር እሸቱ፡- ያጋጠሙን ተግዳሮቶች አሉ። ማዕከሉ በርካታ ስራዎችን እያከናወነ ቢሆንም አሁንም ለተማሪዎች የሚሆን የተሟላ የቤተ ሙከራ እቃዎች በበቂ ሁኔታ አልተሟሉለትም። ለምርምር የሚዉል የተለያዩ መሰረተ ልማቶች አሁንም በበቂ ሁኔታ የሉትም። እነዚህን ዉስንነቶች ለማሟላት ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት እና አጋር አካላት ጋር በመስራት ለሟሟላት ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

አባይ፡- ለነበረን ቆይታ በጋዜጣችን በአባይ እና በአንባቢያችን ስም ከልብ አመሰግናለሁ።

# ዓባይ የቋንቋና የባህል ጥናት ተቋም ሲዳሰስ

በሙሉጎጃም አንዱዓለም

ዐባይ የቋንቋና የባህል ጥናት ተቋም (Abbay, Institute of Language and Culture Studies) አመሰራረቱ፣ራዕዩ፣የትኩረት አቅጣጫው፣ያስመዘገበው ስኬት እና ያጋጠመ ተግዳሮት ሲዳሰስ

አመሰራረቱ በ2004 ዓ.ም ከተቋቋመው "ዐባይ የባህልና ልማት ጥናትና የምርምር ማእከል" እና በ2007 ዓ.ም ደግሞ ከተቋቋመው "የአማርኛ ቋንቋ ማበልጸጊያ ተቋም" በጋራ ጥምረት በ2013 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡ የዚህ ተቋም ራዕይ በአማራ ክልል ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክ በአጠቃላይ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብት ላይ ሳይንሳዊ እና ልማታዊ የሆኑ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ በክልሉ የሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋቸው፣ ባህላዊና ታሪካዊ እሴቶቻቸውና ቅርሶቻቸው ታውቀው፣ ለምተውና ተጠብቀው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅም ሰጥተው፤ እንዲሁም ለትውልድ ተላልፈው ማየት ነው፡፡

በተጨማሪም አማርኛ ቋንቋ የብዙ ኢትዮጵያውያን መግባቢያ ቋንቋነቱ ተጠናክሮ የምርምር፣ የሳይንስና የቴክኖሎጅ ቋንቋ ሆኖ ማየት እንዲሁም በግእዝ እና በሌሎች የውጭ ቋንቋዎች የተጻፉ ጥንታዊ የታሪክ፣የህዋ ሳይንስ፣ የፍልስፍና፣ የህክምና፣ የሥነ ፈለግ፣ የሥነ ምግባር፣ የሥነ እጽዋት፣ የአእዋፍና የእንስሳት፣ መጻሕፍት ወደ አማርኛ ተመልሰው (ተተርጉመው) በየዘርፉ የሚታዩ ክፍተቶች ተደፍነው ማየት ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ ለአማርኛና ለግእዝ ቋንቋዎች እድገት አስተዋጽኦ የሚኖራቸው የምርምር ውጤት ህትመቶች (ጆርናሎች)፣ መጻሕፍት፣ የቃላት ባንክ፣ መዝገበ ቃላት፣ ኢንሳይክሎፒዲያ፣ የተረት፣ የፈሊጣዊ ንግግር፣ የዘይቤዎች፣ የተረትና ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ወዘተ… መድበሎች ተበራክተው ማየት ነው፡፡

የተቋሙ ተልዕኮ የአማራ ክልል ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋ፣ ባህል፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ሥነ ጥበብ፣ ታሪካዊ እሴቶች እና የተፈጥሮ ቅርሶች በሳይንሳዊ መንገድ ተጠንተው፣ ተጠብቀው፣ ተሰንደው ለትውልድ እንዲተላለፉ ማስቻል፣የክልሉን ሕዝብ አገር በቀል ዕውቀቶች፣ ባሕላዊ የዕደ ጥበብ ውጤቶች፣ ልማዳዊና ፎክሎራዊ ሀብቶች በማጥናት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ፣ ታሪካዊ፣ መንፈሳዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶች ባሉበት ሁኔታ እንዲቀጥሉ መንከባከብ፣ መጠበቅና ዕውቅና እንዲያገኙ ማመቻቸት ብሎም የክልሉን ሕዝብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህል በማጥናት በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ እንዲካተትና ማኅበረሰቡ በማንነቱ እንዲኮራና እነዚህን ሀብቶቹን እንዲጠብቅ፤ እንዲንከባከብ ማድረግ ነው፡፡

ተቋሙ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያስመዘገባቸው ስኬቶች ከምርምሩ ዘርፍ 19 ትልልቅ የምርምር ፕሮጀክቶች ተጀምረው አብዛኞቹ የተጠናቀቁ ሲሆን ጥቂቱ በመካሄድ ላይ ናቸው፡፡ ከዐውደ ጥናቶች አንፃር ደግሞ ማዕከሉ ለ4 ዓመታት ግእዝ፣ ለ3 ዓመታት አዝማሪ፣ ለ1 ዓመት መንዙማ (ነሽዳ)፣ ለ6 ተከታታይ ዓመታት ደግሞ ባህልና ሀገር በቀል እውቀቶች ላይ በድምሩ 14 ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ዓመታዊ ዐውደ ጥናቶችን አካሂዷል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ማበልጸጊያ ተቋም 5 ሀገር አቀፍ ዓመታዊ ዐውደ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ከሂዩማኒቲስ ፋኩልቲና ከኢትዮጵያ ቤተ-መጻህፍትና ቤተ-መዛግብት ድርጅት ጋር በመተባበር "ስነቃል ለታሪክ፣ ታሪክ ለስነቃል" በሚል ርእስ ዐውደ ጥናት የተካሄደ ሲሆን በዚህ ዐውደ ጥናት ላይ ተቋሙን በመወከል "የቃል ትረካዎች/Oral Narratives/ ጠቀሜታ፣ እስካሁን የተደረጉ ጥረቶችና የወደፊት አቅጣጫ" በሚል ርእስ ጥናት ቀርቧል፡፡

እንዲሁም "ሀገር በቀል ዕውቀት ለኅብረተሰብ ለውጥ" በሚል ርእስ አገር አቀፍ አውደ ጥናት የተካሄደ ሲሆን፣ከምእራብ ጎጃም ዞንና ከሰከላ ወረዳ አስተዳደሮች ጋር በመተባበር "የሰከላ ወረዳ የቱሪዝም ሀብቶች፣ ፈተናዎችና የባለድርሻ አካላት ሚና" በሚል ርእስ የግማሽ ቀን ዐውደ ጥናት ተካሂዷል፡፡ ከህትመት አንፃር ደግሞ በሁሉም ዐውደ ጥናቶች ላይ የቀረቡ ጥናቶች አርትኦት እየተደረገባቸው መድበለ ጉባኤ ህትመት/Proceeding/ መልክ ታትመዋል፡፡ በተጨማሪም የአማርኛ ቋንቋ የምርምር መጽሔት ቅጽ 1፣በኢትዮጵያ በመካከለኛው ዘመን የነገሱ የአስራ ሶስት ነገሥታት በግእዝ የተጻፉ ጥንታዊ ዜና መዋእሎች ወደ አማርኛ ተተርጉመው፣ የአርትኦት ስራ ተጠናቆ ለኅትመት ተዘጋጅተዋል፡፡ በአቅም ግንባታ በኩል ደግሞ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚናገሩ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ስልጠና እና የሙያ ድጋፍ የተደረገ ሲሆን ከ1ኛ ደረጃ እስከ መሰናዶ ትምህርት ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ለብዙኀን መገናኛና ለህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች፣ለጀማሪ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ለባህልና ቱሪዝም፣ ለሆቴልና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሰራተኞች ሙያዊ ስልጠና ሰጥቷል፡፡

የንባብ ባህልን ለማዳበር የሚረዱ ፋይዳቸው ከፍተኛ የሆኑ መጻሕፍት እየተለዩ፣ በባለሙያ እየተገመገሙ ውይይት ተካሂዶ፣ ጸሐፍቱንም የመሸለም ስነ ስርዓት ተከናውኗል፡፡ ተቋሙ "NORAD" ከተሰኘ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ መነሻ በማድረግ፣ ከደብረ ታቦር ከተማ አስተዳደር ኢንዱስትሪ ልማትና አገልግሎት ጽ/ቤት 13670 ካሬ ቦታ በመረከብ የንባብ አጸድ/Reading park/ ግንባታ ለመጀመር በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከሚገኙ ከሥነልቦና፣ ከታሪክ፣ ከህግ ትምህርት ክፍሎች ጋር በመተባበር ከዓለም ሰራተኞች ማኅበር/International Labour Organization) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ከባሕር ዳር ኢንዱስትሪ ፓርኮች ዘርፍ ኮሚሽን፣ ከአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮና ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የዩኒቨርሲቲና ኢንዱስትሪ ትስስር ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ለውጭ ዜጎች ማሰልጠኛ የሚሆን በአማራክልል ለሚገኙ የውጭ ሀገር ዜጎች የባህል ልውውጥ ተግባቦት ስልጠና /Cross- Cultural Communication Training For Expatriates in Amhara Region"/ የሚል የስልጠና ሞጁል በማዘጋጀት ሞጅሉ አፀድቆ በባሕር ዳር ከተማ ለሚገኙ 24 የውጭ ዜጎች ስልጠና በመስጠትና ስልጠናው በክልሉ በሚገኙ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተደራሽ እንዲሆን፤ ሞጁሉንም በአገር አቀፍ ደረጃ ለማዘጋጀት ማዕከሉ በእቅድ ይዞ እየሰራ ይገኛል፡፡ በአሜሪካ አገር ከተቋቋመ "አድዋ የባህልና የታሪክ ኅብረት" ተቋም ጋር በመተባበር ለባህል አልባሳት አምራቾች፣ ለዲዛይነሮችና ለኪነ ጥበብ ባለሙያዎች "ሴቶች ባህልን ለማሻገር ያላቸው ሚና፣ ከባህላዊ አልባሳት አንጻር" በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዮድ አቢሲኒያ የባህልና የምግብ አዳራሽ የአንድ ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት አስተባባሪነት፣ የሰከላ ልማት ፕሮጀክት፣ በዐባይ የቋንቋና የባህል ጥናት ተቋም ኃላፊነት ወስዶ የባህልና የቱሪዝም ልማት ቡድንን በማቋቋም የባህልና ታሪክ ሙዚየም መመስረቻ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

ለአካባቢው ማኅበረሰብ ክፍሎች ከባህል፣ ከታሪክ፣ ከቅርስ ልማት ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ስልጠናዎች ተሰጥተዋልም በመሰጠትም ላይ ይገኛል፡፡

የትምህርት ዕድል ከመስጠት አኳያ ከ"NORAD" ጋር በመተባበር ከ1ኛ ደረጃ እስከ መሰናዶ ትምህርት ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን 18 በሁለተኛ ዲግሪ ያጠናቀቁ ሲሆን ሁለት ደግሞ የሶስተኛ ዲግሪአቸውን በመማር ላይ ላሉ የትምህርት እድል አግኝተዋል፡፡

የትኩረት አቅጣጫውም በአማርኛ ቋንቋና በክልሉ ሕዝብ ባህሎች ልማት ላይ ያተኮሩ ስራዎችን ለማከናወን ያለመ ስለሆነ የአማራ ሕዝብ የዳበረ ቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክና ሥነ ጥበብ (ሙዚቃ፣ ስእል፣ ሥነ ጽሑፍና ቅርጻቅርጽ) ካላቸው የኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል አንዱ መሆኑን አጉልቶ ያሳያል፡፡

ተቋሙን ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከሉላዊነት እና ከዘመናዊ ቴክኖሎጅ መስፋፋት ጋር ተያይዞ በቋንቋዎች የንግግርና የጽሕፈት አጠቃቀም ሥርዓት ላይ በርካታ ጫናዎች እየደረሱ ይገኛል፡፡

ወደ ገጽ 9 የዞረ

## ስብጥር

# አንዱ ክፍል (ወግ)

በሳምራዊት አበባየሁ
የሲኒማና ቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የ2ኛ ዓመት ተማሪ

መኪና ውስጥ ነኝ፡፡ ጉዞየን ወደ አዲስ አበባ እሄድሁ ነው፡፡ ቤቴን፣ቤተሰቤን፣ጓደኞቸን፣ትምህርት ቤቴን ያደግሁበትን ከተማ ጥዬ እየሄድሁ ነው፡፡

ከዚህ በፊት ዘመድ ጥየቃ ወይም ደግሞ ክረምቱን እዛ ለማሳለፍ አንዳንዴ የምሄድባት አዲስ አበባ አሁን ግን ላልተወሰነ ጊዜ ኑሮየን ከዛ ላደርግ እየሄድሁ ነው፡፡ ለትምህርቴም ሆነ ህይወቴን ለማስቀጠል ግድ ስለሆነብኝ እንጅ ጥያቸው ሄጄ እንኳን አመታትን ላስቆጥር ይቅርና ለቀናትም ቢሆን ከነሱ መለየት አልፈልግም ነበር፡፡

ራሄል እባላለሁ፡፡ የ10ኛ ክፍል ትምህርቴን አጠናቅቄ ወደ 11ኛ ክፍል አልፌአለሁ፡፡ የቤታችን ስድስተኛ ልጅ ነኝ፡፡ አጠቃላይ ዘጠኝ ነን፡፡ ሶስት ወንድ፣ ስድስት ሴት፡፡ የአብዛኞቻችን የእድሜ ልዩነት ልክ እንደ እጅ ጣቶች ነው፡፡ ብዙም አንራራቅም፡፡ አስራአንድ አመቴ እያለ ነበር አንዱ እድሜው ከኔ በጣም የበለጠ በጊዜው ወጣት የሚባል እድሜው 26 የሚሆን ልጃችሁን ዳሩልኝ ብሎ ቤተሰቦቸ ጋር የመጣው፡፡ እኔ በዚያን ጊዜ እንኳን ስለ ትዳር ላውቅ ይቅርና እቃቃ ተጫውቸ አልጨረስሁም ነበር፡፡

እናቴ ካደገችበት ማህበርሰብ አንፃር ስለምታስብ ተስማማች፡፡ በሷ አባባል ‹‹የሴት ልጅ የመጀመሪያ እድል ካለፋት ጥሩ አይደለም እሱ ካመለጣት ድጋሜ አታገባም›› ብላ ታምናለች፡፡ አባቴ ግን እንደሷ አይደለም፡፡ የእሱ ዋነኛው ሃሳብ ሁልጊዜ የሚነገረን ነገር ‹‹ ሴት ልጅ ተምራ የራሷ ስራ ሊኖራት ይገባል›› ይላል፡፡ እናቴ አይሆንም ብላ ጥሎሹን ተቀበለች፡፡ አባቴም ውሳኔውን ሰጠ፡፡ ‹‹ፈቅጃለሁ ግን የምታገባው ትምህርቷን ጨርሳ ነው፡፡ እስከዚያው ከዚህ ከቤተሰቦቿ ጋር ነው የምትኖረው›› አለ፡፡ በውሳኔውም ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡

ልክ 10ኛ ክፍል ልጨርስ አካባቢ ሰውየው ከቤተሰቡ ጋር መጥተው እሱ ጋር እየኖርሁ እንድማር እንደሚፈልግ ተናገሩ፡፡ የዚያን ጊዜ እድሜየም ከፍ ስላለ ብዙ ነገር እረዳ ነበር፡፡ ስሰማ አላመንሁም ነበረ፡፡ ስለትዳር አስቤ እንኳን የማላውቅ ልጅ ልታገቢ እኮ ነው እያሉ ሲያወሩ መቀበል አቃተኝ፡፡ አልቻልኩም፡፡ እናቴ ውሳኔዋን ወስናለች፡፡ በሷ በኩል ምንም ልቀይር እንደማልችል አውቀዋለሁ፡፡ ግን አባቴ መጨከኑን መቀበል አልቻልሁም፡፡ ምንም እንደማትቀይር፣ በምንም እንደማላሳምናት ባውቅም እናቴን ተማፅኛት ነበር፡፡ ለክፋት እንዳልሆነ አውቃለሁ፡፡ ሳላገባ እንዳልቀርባት ፈርታ መሆኑን እረዳለሁ፡፡ የዚያን ሰሞን ምግብ አስጠላኝ፡፡ ሳቅ ጨዋታየ ከፊቴ ተገፈፈ፡፡ አንድ ቀን አባቴ ከስራ ከገባ በኋላ አስጠርቶኝ ስሄድ ሳሎን ቁጭ ብሏል፡፡ አባቴ የኔ አባ'ቢ ምን አይነት ሰው መሰላችሁ? እረጅም የኔ ቁመተ ሎጋ ፊቱ አይፈታም፡፡ ኮስተር ፣ኮፍጠን ያለ ኮስታራ ነው፡፡ ለልጆቹ፣ ለቤተሰቦቹ ሚች፣ ለቤተስቡ ጋሻ ነው፡፡ እና የዚያን ቀን ‹‹ቀና በይ! የማናግርሽ ጉዳይ አለኝ! አሁን አንች ትንሽ ልጅ አይደለሽም… ባንች ጉዳይ እኔ ብቻ ሳልሆን አንችንም ማማከር ይኖርብኛል፡፡

ስለዚህ አንድ ነገር ብቻ ንገሪኝ፡፡ ማግባት ትፍልጊያለሽ?›› አለኝ፡፡ ከየት እንደመጣ ሳላውቀው እንባየ ዱብ ዱብ እያለ፡፡ ወዲያው ‹‹ አይ አይ አይ ›› አልኩት ‹‹እሽ አንች ሳትፈቅጅ ምንም የሚፈጠር የለም›› አለኝ፡፡ አቤት ተስፋ… ልክ ይሄ ቃል ከሱ ሲወጣ የሆነ ነገር ከላዬ ላይ የወረደ መሰለኝ፡፡ ሰላሜ የተመለሰ መሰለኝ፡ አባ'ቢ አደርጋለሁ ካለ እንደሚያደርግ አውቀዋለሁ፡፡ ግን በዛው ልክ ሰዎቹም አልሰማም አሉ፡፡ መማር ካለባት ከዚህ በኋላ ከኔጋ እየኖረች ትማራለች እንጅ አይሆንም አሉ፡፡ አባቴ የነበረው አንድ ምርጫ ብቻ ነበር፡፡ እኔን ከዛ ከተማ ማስወጣት፡፡ ለዚያ ነው አሁን ወደ ሸገር እየኮበለልሁ ያለሁት፡፡

ምርጫ ቢያጣ ነው እንጅ፣ አባ'ቢ ከስሩ እንድወጣ እራሱ አይፈልግም ነበር፡፡ ሰውየው ከነቤተሰቡ ሲመጣ አባ'ቢ ‹‹ይኸው ተው እያልኳችሁ እኔንም ጥላኝ ጠፋች›› አላቸው፡፡ አላመኑትም፡፡ ሊዋጥላቸው አልቻለም፡፡ጥሎሻቸውን እንደሚመልስላቸው እና ስለልጄ ዳግመኛ እንዳታነሱብኝ ብሎ ሸኛቸው፡፡

በዚህ ምክንያት ነው እንግዲህ ቤተሰቤን፣ የኖርሁባትን ከተማየን ጥዬ እየሄድሁ ያለሁት፡፡ የምሄድበት ቤት የስጋ ዝምድና የለንም፡፡ ግን ደግሞ ቤተሰብ ለቤተስብ ትውውቃችን እና ቀረቤታችን ትልቅ ነበር፡፡ ለዛ ነው፣ ወደዚያ የላኩኝ፡፡ አሁን የምሄድበት ቤተሰብ 5 ወንድ እና 3 ሴት ልጆች አሏቸው፡፡ አሁን ላይ ግን ቤት ያሉት ሶስቱ ሴቶች እና ሁለቱ ወንዶች ናቸው፡፡ ከሶስቱ ሴቶች አንዷ የኔ እኩያ ናት፡፡ ከሁለቱ አንዱ ወንድ የአዕምሮ እድገት ውስንነት ታማሚ ነው፡፡ አንዱ እድሜው 24 ይሆናል፡፡ ናታን ይባላል፡፡ ስደርስ ጥሩ አቀባበል ነበራቸው፡፡ ከቤተሰብ ተለይቸ ብመጣም በምክንያት እና ለዓላማ ስለሆነ እራሴን ማጠናከር እንዳለብኝ አሰብሁ፡፡ ቤቱ የቤተሰብ የጋራ መኖሪያ አይነት ነው፡፡ የኛ አንደኛ ፎቅ ላይ ነው፡፡ ከኛ በላይ ሌሎች ሁለት ቤተሰቦች አሉ፡፡ ትምህርት ቤት ተምዝግቤ ትምህርቴን ጀመርሁ፡፡ የተመዘገብሁበት ትምህርት ቤት መነን ይባላል፡፡ አስራ አንደኛ ክፍል ነው የገባሁት፡፡ የኔ እኩያ የቤቱ ልጅ ሜላት ትባላለች፡፡ አስረኛ ክፍል ተማሪ ናት፡፡ ያን ያህል ባይሆንም ከኔ የሚሻል ሞላ ያለ ሰውነት አላት፡፡ የኔን ቅጥነት ተውት፡፡ ሰው ከሩቁ ትኩር ብሎ ካላየኝ ወደ ፊት ልምጣ ወደ ላይ ልመለስ አልለይም፡፡ የቆዳ ቀለሜ ቀይ ነው፡፡ ፀጉሬ ልክ እንደ ቁመቴ እረዘም ያለ በአባቴ የወጣሁ ኮስታራ ነኝ፡፡ ቀስ በቀስ አካባቢየን እና ትምህርት ቤቴን እየለመድሁት መጣሁ፡፡

ከቤተሰቡምጋርያለኝግንኙነትጥሩነበረ፡፡ ሜላት ከኔ ፈጠን ያለች እና ችኩል ናት፡፡ እኔ ግን በባህሪየ ቁጥብ እና ተጠራጣሪ ነኝ፡፡ ሰው ከተግባባሁ በኋላ ግን ተጫዋች ነኝ፡፡ እስክንግባባ ድረስ ነው እንጅ፡፡ መልኬ ላይ አዲስነቴ ተጨምሮ በሰፈርም በትምህርት ቤትም ላናግርሽ፣ ልሸኝሽ የሚሉ በርካቶች ነበሩ፡፡ እኔ አላስጠጋም እንጅ፡፡ በሰፈራችን አንዳንዴ ሰብሰብ ብለው የሚቀመጡ ጎረምሶች ነበሩ፡፡ ከዛ ውስጥ አንዱ የኛ መኖሪያ ቤት ህንፃ ላይ የሚኖረው ናሆም ነው፡፡ የማውቀው ከዛው ህንፃ ላይ ስንወጣ ስለምንገኛኝ ነው፡፡ ከአይን ሰላምታ ውጭ ሌላ ግንኙነት የለንም፡፡

ወይኔ---- መልክ ግን የግሉ ነው፡፡ አቤት ቁመና! አቤት ቁንጅና! አቤት ፈገግ ሲልማ…! እንዲህ እንዲህ ተብሎ አይገለፅም፡፡ በቃ ቆንጆ ነው፡፡ ግን ምን ዋጋ አለው ሱሰኛ ነው፡፡ ያጨሳል፡፡ በህይወቴ በጣም የሚያበሳጨኝ እና የሚያስጠላኝ ነገር ሱስ ነው፡፡ እድሜው 24 አካባቢ ነው፡፡ የናታን እኩያ ነው፡፡ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን አጠናቆ ተመርቋል፡፡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለ ትምህርት ቤቱ ተወዳድሮ Mr. HANDSOME ተብሎ ተሸልሟል፡፡ ናታን ጋር አንዳንዴ ቤት ብቅ ይላል፡፡ ናታንም ያጨሳል፡፡

ግን ከቤት ማንም የሚያውቅ የለም፡፡ ስለሱ ሲነሳ ‹‹የኔ ጨዋ የቤተ-ክርስትያን ሰው›› ነው የሚሉት፡፡ አይ ናታን!! ናሆም ደስ የሚል ልጅ ነው፡፡ ቀስ በቀስ መግባባት ጀመርን፡፡ የኔ ቅርበት ጓደኝነት ብቻ ነበር፡፡ የሱ ግን ቀስ በቀስ ስሜቱ እየተቀየረ መጣ፡፡ ትምህርት ቤት የምሄደው በታክሲ ነበር፡፡ ግን ከሆነ ጊዜ በኋላ ልክ ትምህርት ቤት ልሄድ ከቤት ስወጣ ናሆም ቀድሞ ውጭ ይጠብቀኛል፡፡ ታክሲ ልይዝ ስል አይቻልም ብሎ እየጎተተ ይወስደኛል፡፡ ፈርጠም ያለ ሰውነት ስላላው በዛ ቅጥነቴ ከእሱ ማምለጥ ለእኔ የማይታሰብ ነው፡፡ አይ ፍርጃየ… ከቤት እስከ ትምህርት ቤት በእግሬ ያስኬደኛል፡፡ ስሄድ ብቻ ቢሆን ጥሩ ነበር፡፡ ነገር ግን ክፍለ ጊዜው አልቆ ከትምህርት ቤት ስወጣም ጋሽ ናሆም በር ላይ ይጠብቀኛል፡፡ ሳልወድ በግዴ ያንን መንገድ እመለሰዋለሁ፡፡ ናሆም በተደጋጋሚ እንደሚወደኝ ነግሮኛል፡፡ እኔ ግን ከጓደኝነት ያለፈ በእኔና በእሱ መካከል መቸም ምንም ሊኖር እንደማይችል ነግሬዋለሁ፡፡ ሁኔታየ እልህ ያስይዘዋል፡፡ በሰፈሩ ይፈለጋል፣ በሴቶች ይፈለጋል፣ እንኳን አናግሮ ጠይቆ አይደለም ሴቶቹ ናቸው የሚፈልጉት፡፡

እኔ ራሄል ግን ወይ ፍንክች፡፡ ይሄ ነገሬ መሰለኝ ይበልጥ የሚያበሳጨው፡፡ አብረን እየሄድን ገና ሲጠጋኝ ‹‹አይ አትጠጋኝ በናትህ ትሸታለህ እኔ የሚያጨስ ሰው ሽታ አልወድም ያስመልስኛል›› እለዋለሁ፡፡ እንደዛ ስለው አይችልም፡፡ በፈረጠመ እጁ ቀጭን ትክሻየን ድርግም አድርጎ ይመታኛል፡፡ በሱ ምክንያት ከሆነ ጊዜ በኋላ እጀ የሚሰራ አይመስለኝም፡፡ ሳናድደው እልህ ሳስይዘው እኔን መምታት ነው የሚቀለው፡፡ ‹‹አንች ልጅ እኔ አላጨስም ስርዓት ያዥ›› ይለኛል፡፡ በጣም የሰለቸኝ ነገር ከትምህርት ቤት ወደ ቤት፣ ከቤት ወደ ትምህርት ቤት በእግሬ የምመላለሰው ነገር ግን ሁሌ የታክሲ ብር ይዤ እወጣለሁ፣ ይዤው እመለሳለሁ፡፡ ከሆነ ጊዜ በኋላ ፀሎቴ ‹‹ ምናለ ዛሬ ተኝቶ ባረፈደ ወይ በቀደምሁት›› ነበር፡፡ እሱ ግን ወይ ጉድ ነጋ አልነጋ ብሎ ከዛች ቦታ ላይ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ናሆም የሚቀርበኝን ያህልም ይፈራኛል፡፡

እኛ ቤት የምትሰራ አንድ ልጅ ነበረች፡፡ ብስራት ትባላለች፡፡ መልካም ሴት ናት፡፡ ደግሞ የኛ ከተማ ሴት ናት፡፡ ስለኔ ክፉ እንዲነሳ አትፈልግም፡፡ ሁሌም ትመክረኛለች፡፡ ትቆጣኛለች፣ ደግሞ ትወደኛለች፡፡ እኔም በጣም ነው የምወዳት፡፡ አንድ ቀን ምሽት ሱቅ ተልካ አብሬያት ወጣሁና መንገድ ላይ እየሄድን አንድ ሰው አየን፡፡ ጨለማ ነው፡፡ ግን ናሆም መሆኑን አውቂያለሁ፡፡ እያጨሰ ነበር፡፡ አላየኝም ነበር፡፡ ልክ እሷ እሱ

# አንዱ ክፍል (ወግ) ----ከገጽ 6 የዞረ

መሆኑን ስታውቅ ‹‹ሰላም አመሸህ ናሆም›› አለችው፡፡ ልክ እንዳየን እያጨሰ የነበረውን ሲጋራ ፍም በጣቶቹ ጥብቅ አድርጎ ያዘው፡ ፡ መንፈስ ያየ ነበር የሚመስለው፡፡ ክው ብሎ ‹‹ ደና አደራችሁ›› አለን፡ ፡ ምን እንዳስደነገጠው ገብቶኛል፡ ፡ ዝም ብየው አለፍኩ፡፡ እንደዚህ እንደዚያ እያለ ጊዜያት አለፉ፡፡ አንድ ቀን ናሆም ለአንድ ጓደኛው አስተዋወቀኝ፡፡ የሱ ጓደኛ ስለሆነ ተዋወቅሁት የዚያን ቀን ከነሱ ጋር ነው ከትምህርት ቤት የተመለስሁት፡ ፡ በነጋታው የሆነ ስልክ ተደወለልኝ፡ ፡ ሳነሳው የናሆም ጓደኛ ነበር፡፡ ብቻችንን እንድንገናኝ እንደሚፈልግ እና የምንገናኝበትን ቦታ ነገረኝ፡፡ ዝም አልሁኝ፡፡ አልሄድሁም፡፡ ከዛ በኋላ ደጋግሞ ጠየቀኝ፡፡ እረፍት ነሳኝ፡፡ ሲበዛ እሺ አል፡፡ ‹‹ ጭራሽ እራሴ አስተዋውቄ ሊበላኝ›› ብሎ ሄደ፡ ፡ ከዛ በኋላ ጓደኛው ይሙት ይኑር አላውቅም፡፡ ከናሆሜ ጋር በጣም ተቀራረብን የሱ ስሜት እንዳለ ሁኖ የኔ ግን ምርጥ ጓደኛ ነበር፡፡

ተስማምተን አናውቅም፡፡ ሁሌም እንጨቃጨቃለን፡፡ እሱ በዛ እጁ አንዴ ትክሻየን አንዴ ጀርባየን እንዳቀላው ነበር፡፡ የሚያም አይመስለውም መሰለኝ፡፡ ከቤት ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ የናታን ሁኔታ እየተቀየረ ነበር፡፡ እንደወንድሜ የማየው ሰውየ ለኔ የተለየ ስሜት እንዳለው በግልፅ እያስታወቀበት መጣ፡፡ ይህን ያዩ ቤተሰቦቼ እኔ ላይ መቀየር ጀመሩ፡፡ አንድ ያልነገርኋችሁ ነገር በህይወቴ ናሆምን ለማግኜት ብየ ከቤት ወጥቸ አላውቅም፡፡ በቃ ይሄን የትምህርት ቤት መንገድ እየጠፈጠፈ ይወስደኛል፣ ይመልሰኛል፡፡

ከቤት ውስጥ ያለው ሁኔታ እንዳለ ተቀየረ፡፡ ግልምጫቸው በረታብኝ፡ ፡ ምን እንደተፈጠረ ግራ ግባኝ፡፡ ለካ እነሱ በናታን ምክንያት ነው፡፡ ‹‹ይሄን ምንም የማያውቅ ልጅ ምን እስነክታው ነው? ድሮም ገና ስትመጣ አላማርችኝም›› መባል ተጀመረ፡፡ አንድ ቀን ቤት ውስጥ የቤተሰብ ስብስባ አለ አሉና እኔን እንደማያካትት ነገሩኝ፡፡ በስመአብ! ያስብላል የምር፡ ፡ አንድም ቀን ከቤተሰቤ ነጥየ አይቻቸው አላውቅም ነበር፡፡ ሴቶቹን እህቴ፤ ወንዶቹን ደግሞ ወንድሜ እያልኩ ነበር የምጠራቸው፡፡ እነሱ ግን ያን ሁሉ ትተው ባዳነቴን አስተወሱ፡፡ ግልፅ በሆነ ቃል ባዳ ነሽ የኛ ቤተሰብ አይደለሽም አሉኝ፡፡

በስብሰባው ስለኔ ነበር ሲተካተኩ የዋሉ፡፡ ጥዋት ትምህርት ቤት ከመሄዴ በፊት ቤት ውስጥ የሚሰራ ስራ ብስራትን እያገዝሁ እንድሰራ ተደረግኩኝ፡፡ በወጣሁ በገባሁ ቁጥር ሁሌ በአሽሙር እንደተናገሩኝ ነበር፡ ፡ ቆይ እኔ ምን አደረግሁ? እንዴ! ‹‹ይች ዱርዬ ለራሷ የተበላሸች ምንም የማያውቀውን የቤት ልጅ ታበላሸው›› እያሉ ይዘባበቱብኛል፡፡ እንኳን ተናግረውኝ ድሮም ሆድ የባሰኝ ሰው ነኝ፡፡ እንኳን ይሄ ተጨምሮ ድሮም የሰው ቤት የሰው ነው መቸም እንደራስ አይሆንም፡ ፡ ወይኔ እማየ ጮክ ብዬ መናገር ይቅርና ማልቀስ እራሱ አልቻልሁም፡፡ የእናቴ ጉያ ናፈቀኝ፡፡ ከእሷ ገብቸ ማልቀስ አማረኝ፡፡ ጠረኗን ፈለግሁት፡ ፡ ምን አለ አንዴ አይዞሽ ልጀ እያለች በእጆቿ በዳበሰችኝ አልኩ፡፡ ቀን በቀን ለቅሶ ሆነ ስራየ፡፡ ተነስቸ ወደ ቤቴ እንዳልሄድ ትምህርቴን ምን ላድርገው፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን እሱን እንኳን በስነ-ስርአት መከታተል አቃተኝ፡፡ ናሆም ሰላም እንዳልሆንሁ በሁኔታየ ገብቶታል፡፡ የሆነ ቀን ለጥምቀት እኔ እና ሜሉ ታቦት ለመሸኘት አንድ ላይ ወጣን፡፡

ናሆምን እና ጓደኛውን አግኝተናቸው አብረውን ነበሩ፡፡ ሸኝተን ስንመለስ ዛሬ ሳንጋብዛችሁ አትመለሱም አሉን፡ ፡ እኔ አልፈልግም ብዬ ኮስተር አልኩ፡፡ ሜሉ ግን ምን ችግር አለው ጎረቤታችን አይደል እንዴ ብላ ይዛኝ ገባች፡፡ አንድ ሆቴል ገባን፡፡ በላን፡ ፡ ከዛ መጠጣት ተጀመረ፡፡ እኔ አንድ ቢራ አስከፍቸ ቁጭ አልሁ፡፡ እሱን እራሱ ግማሽ አላደረስኩትም፡ ፡ ሜሉ ግን እንዲያው ስትገለብጥ ነበር፡፡ ሳናውቀው ስዓቱ አንድ ስዓት ሆነ፡፡ ደንግጬ ተነሳሁ፡፡ ወጣን፡ ፡ ሜላት ሰክራ ሞቅ ብሏት ነበር፡ ፡ እቤት ስንደርስ 1:30 ይሆናል፡ ፡ አበቃልኝ አልኩ፡፡ እንኳን ይሄን አይተውብኝ ድሮም ይዘውኛል፡፡ ገና ከመግባታችን በዱላ ነበር የተቀበሉን፡፡

አቤት የተገረፍነው ግርፊያ መቸም አልረሳውም፡፡ መጀመሪያም ያደረግነው ነገር በእሳት ላይ ጋዝ ማርክፍከፍ እንደሆነ ታውቆኛል፡ ፡ እንዳልኩትም ነገሩ ሁሉ ተጠምዝዞ ወደኔ ዞረ፡፡ ‹‹ ጭራሽ ብለሽ ብለሽ ምንም የማታውቀውን ልጅ አበላሸሻት፡፡ አስመሸሻት አሉ፡፡ አልበቃ ብሎሽ አስክረሽ አመጣሻት፡ ፡ ሌላ ነገር አድርገሻት ቢሆን ምን ይታወቃል›› እያሉ የስድብ ማት አወረዱብኝ፡፡ ምንም ቢፈጠር እኔ ነኝ ጥፋተኛዋ፡፡ እነሱ ጋር ሲደርስ ሁሌም ባለጌዋ እኔ ነኝ፡፡ ምንም እንደዚያ ቢሉኝ እኔ ግን ተቆንጥጬ ያደግሁ ጨዋ የጨዋ ልጅ ነኝ፡፡

ከቀን ወደ ቀን ቤቱ ውስጥ ያለው ነገር እየበረታብኝ መጣ፡፡ አልቻልኩም፡ ፡ የምር አቃተኝ፡፡ ያልሆንሁትን ሆንሽ መባል በወጣሁ በገባሁ ቁጥር የምሰማው ንግግር ከበደኝ፡ ፡ ‹‹አባብዬ የኔ አባት የት ነህ?›› አልኩ፡፡ ‹‹ሲናገሩኝ አይደለም ቀና ብለው እንዲያዩኝ የማትፈቅደው አባቴ የት ነህ?›› አልኩኝ፡፡ አይ ችግር አይጥሉ አጣጣል ይጥላል፡፡

የተፈጠረው ተፈጥሮ እዚህ ባልመጣ ኖሮ እንዲያ ባልተናገሩኝ ነበር፡ ፡ ብስራት እንደዚህ አምሽቸ ስገባ ተናደደች፡፡ ከምንም በላይ እነሱ የሚናገሩኝ ንግግር ያበሳጨታል፡፡ ሁሌም የምትለኝ ነገር ‹‹እኔ በደንብ አውቅሻለሁ የኔ ጨዋ ሰው›› የነሱ እንደዚያ መሆን ሳይበቃኝ የናታንም ሁኔታ እየባሰ መጣ፡፡ የሁልጊዜ ንግግሩ ‹‹ አገባሻለሁ›› ነው፡ ፡ ናታን የናሆም አልፎ አልፎ ክሱ ጋር ከቤት መምጣት ያበሳጨው ጀመረ፡፡ ‹‹አትምጣብኝ›› ሊለው ምንም አይቀረውም፡፡ የሜላት እና የናታን ነገር ተደራርቦ ቤተሰቡ የእግር እሳት ሆኑብኝ፡፡ ድሮ በትምህርት ቤቴ ተጠሪ ተማሪ ነበርኩ፡፡ አሁን ግን ያ… ሁሉ ገደል ገባ፡፡ የቤተሰብ ናፍቆት፡ ስድብም ግልምጫው ብቻ ምኑ ቅጡ፡፡ አልፎ አልፎ ትምህርት ቤት እቀራለሁ፡፡

ብሄድም በስነ-ስርዓት መከታተል ከበደኝ፡፡ ከቤት ተመልሶ ማንበብ የሚባለው ነገር እኔ ጋር ታሪክ ሆነ፡ ፡ ትምህርት የቀጣሁ ቀን ናሆም ናታንን ለመጠየቅ በሚመስል ሰበብ ቤት ሰተት ብሎ ይመጣል፡፡ የአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና እየደረሰ ነው፡፡ ማለፍ እፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም ህልም አለኝ፡፡ እራሴን አስቀምጨ ስሰራው የኖርሁት ቦታ አለኝ፡፡ ያባቴን ፍላጎት እውን እንዲሆን እፈልጋለሁ፡፡ ግን በየት በኩል፡፡ መቸ የተማርሁትን መቸ ያነበብሁትን ነው ተፈትኘ የማልፈው? ፈተናው ደርሶ ተፈተንሁኝ፡፡ እንዳልሰራሁ ባውቅም ግን ትንሽ ተስፋ ነበረኝ፡፡

ከምንም በላይ የማስበው ግን ከዛ ቤት የምወጣበትን ቀን ነበር፡፡ ውጤት ተለቀቀ፡፡ አላለፍኩም፡፡ ህልሜ ቆመ መሰለኝ ህሳቤ ምኞቴ ሁሉም ገደል የገባ መሰለኝ፡፡ ቤተሰቤን ያዋረድሁ መሰለኝ፡፡ ድንገት ዝም… ፀጥ…መውደቄን ሲሰሙ እቤት ውስጥ ተሳለቁብኝ፡፡ ለነገሩ ከየት አምጥተሽ ታልፊዋለሽ? ዙረቱን ማን ይዙርልሽ? ማን ይቦዝንልሽ? እያሉ በነገር ይወጉኛል፡፡ ለትንሽ ጊዜ እራሴን ማረጋጋት አልቻልሁም ነበር፡፡ ናሆም ቤት ይመላለሳል፡፡ እኔ ትዝም አላለኝ፡፡

አንድ ቀን ቁጭ ብየ አሰብሁት፡ ፡ ለምንድነው እዚህ ያለሁት ትምህርቴም አልቋል! አብቅቷል! እቤቴ ያለውን ነገር አባቴ አስተካክሎታል፡፡ ሳስበው ምንም ከዚህ ቤት እንድቆይ የሚይዘኝ ነገር የለም፡፡ ደግሜ እራሱ አላሰብሁትም፡ ፡ ተነስቸ ሻንጣየን ማስተካከል ጀመርሁ፡፡ አባቴን የመጓጓዣ ገንዘብ እንዲልክልኝ ነገርሁት፡፡ ላከለኝ፡ ፡ ምንም አላልኳቸውም፡፡ አንድ የተናገርሁት ነገር ቢኖር ‹‹ልሄድ ነው ›› የሚል ቃል ብቻ ነበር፡፡ ማንም እንዲያስቀመኝ አልፈቀድሁም ነበር፡፡ ሻንጣየን ይዤ ወጣሁ፡፡

ናታን አይሆንም እያለ ከእነሱ ጋር ሲከራከር እሰማዋለሁ እንዴት ‹‹ዝም ትሏታላችሁ ልሄድ ነው ስትል እንዴት ትፈቅዱላታላችሁ›› እያለ ይጮሀል፡፡ እነሱ ላይ የሚጮኸው እኔን ማስቆም ኃይል እንደሌለው ስለሚያውቅ ነው፡ ፡ ‹‹ ቀልደኛ ደሞ አገባሻለሁ ይላል እንዴ!›› እያልኩ በውስጤ ወጣሁ፡፡ ወደ ቤቴ፤ ወደ ቤተሰቦቼ፤ ወደ ከተማዬ፤ ወደ እናቴ ቤት ልመለስ ነው፡፡ በትምህርት መውደቄ ያሳለፍሁት ነገር ሁሉ አልታይሽ አለኝ፡፡ አንድ እና አንድ የማስበው ነገር ሂጀ የአባቴ ስር ውስጥ መግባት ብቻ ነበር ለሚያየኝ፡፡

የታሰርሁበት ካቴና ተፍቶልኝ ነፃ የወጣሁ ሰው እመስላለሁ፡፡ ሄድሁኝ ቤቴ፡፡ ነፃነቴ ሁሉ ተመለሰልኝ፡፡ ዳግም ልጅ ሆንሁ፡፡ እናቴን አቅፌ ስቅስቅ ብየ አለቀስሁ፡፡ ያባቴን ኮስታራ ፊት ሳይ ከዚህ በኋላ ማንም እንደማይነካኝ ተሰማኝ፡፡ ኩራቴና ወኔየ ተመለሰ፡፡ ለአባቴ መውደቄን ስነግረው ‹‹ህይወት በዚህ አይቆምም ትማሪያለሽ›› አለኝ፡፡

አባቴ ለትምህርት መቸም ተስፋ አይቆርጥም፡፡ እነሱ ጋር ከሆንሁ እንኳን ትምህርት ሌላም ነገር ቢሆን እንደምወጣው አውቃለሁ፡፡ አንድ ቀን በር ተንኳኩቶ የሆነ ትንሽ ልጅ ደብዳቤ ሰጥቶኝ ሄደ፡፡ ናሆም ነበር፡፡ ወይ ጉድ… ተከትሎኝ መምጣቱን ላምን አልቻልሁም፡፡ ናሆም በህይወቱ ከአዲስ አበባ ወጥቶ አያውቅም ነበር፡፡ ደብዳቤው ላይ አግኝቶኝ ሊያናግረኝ እንደሚፈልግ እና ያለበትን ቦታ ፅፎታል፡፡

እኔም እንዳማላገኜው እና ወደ ሀገሩ እንዲመለስ፣ እኔ ላይ ባለው ስሜት ተስፋ እንዲቆርጥ ፅፌ ላክሁለት፡ ፡ ህይወቴን እንደ አዲስ ጀመርኩ፡ ፡ በአዲስ ተስፋ እና በአዲስ ወኔ ያለፈው ሁሉ ለኔ እንደ ትምህርት ሆኖ ላይፋቅ በውስጤ እንደ ጠባሳ ለዘላለም ይቀመጣል፡፡

---ተፈጸመ---

# የፔዳጎጂና ትምህርት ምርምር ተቋም አሁናዊ ቁመና

በሙሉጌታ ዘለቀ

ምርምር አዳዲስ እውቀት፣ ቴክኖሎጂና አስተሳሰብ ለመፍጠር፣ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታትና ሁለንተናዊ የማህበረሰብ ልማትን ለማፋጠን ሲባል የሚከናወን ሳይንሳዊና ስልታዊ ተግባር ነው፡፡ የበለጸጉ አገራት ታሪክ እንደሚያሳየን ያለምርምር ፈጣንና አስተማማኝ እድገት እውን ሊሆን አይችልም፡፡

የትምህርት ሴክተር በአንድ ሀገር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካ ህይዎት ውስጥ ንቁና ውጤታማ ተሳትፎ ማድረግ የሚችሉ ብቁ ዜጎችን የማፍራት ትልቅ ማህበራዊ ሀላፊነት አለበት፡፡ ይሁን እንጂ ዘርፉ ይህን ቁልፍ ሀላፊነት በሚፈለገው መንገድ መወጣት እንዳይችል እየደረጉ ያሉ በርካታ ችግሮች አሉበት፡ ፡ እነዚህ ችግሮች ሳንሳዊና ስልታዊ በሆነ መንገድ ካልተፈቱ የሴክተሩ ብቁ ዜጋ የመፍጠር ራዕይ እውን ሊሆን አይችልም፡፡

በዚህም የተነሳ በርካታ አገሮች ለትምህርት ምርምር ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ የምርምር ተቋማትን በመመስረትና ተቋማቱን በተፈላጊዉ የሰው ኃይል፣ ቁሳቁስና በጀት በማደራጀት የትምህርት ዘርፍን ችግሮች በመፍታት ትምህርት የሁለገብ ልማት ማሳለጫ መሳሪያ እንዲሆን በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ እውቅ የምርምር ዩኒቨርስቲ ለመሆን ያለውን ራዕይ ለማሳካት የምርምር ተቋማትን የመሰረተ ሲሆን ከእነዚህ መካከል አንዱ የፔዳጎጂና ትምህርት ምርምር ተቋም ነው፡፡

ይህ ተቋም ዋና አላማ አድርጎ የተነሳዉ በትምህርት ዘርፍ ለሚከናወኑ ተግባራትና ለሚታዩ ችግሮች በምርምር የተደገፉ ምክረሃሳቦችን ከማቅረብ ባሻገር የስነ ትምህርት የዕዉቀት መስክን የሚያዳብሩ የምርምር ስራዎችን ማካሄድ ነው፡፡ በዚህ አጭር ጹሁፍ ተቋሙን የተመለከቱ አንዳንድ መሰረታዊ ጉዳዮችን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

የፔዳጎጂና ትምህርት ምርምር ተቋም ምስረታ በሀገራችን የሚገኙ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ጥራት ያለው የማስተማር አገልግሎት የመስጠት፣ ችግር ፈቺ ምርምር የማካሄድና በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶች ላይ የመሳተፍ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከተመሠረተ ጀምሮ እነዚህን ተቋማዊ ኃላፊነቶች ለመወጣት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ለዚህም ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የትምህርት እና የምርምር ክፍሎችን አቋቁሟል፡፡

የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም ዩኒቨርሲቲው በምሥረታ ጊዜው ካቋቋማቸው ጥቂት የምርምር ተቋማት አንዱ ነው፡፡ ተቋሙ አሁን የሚጠራበትን ስያሜ ይዞ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የተመሰረተው በ2005 ዓ.ም ቢሆንም በትምህርትና ስነ-ባሕሪ ሳይንስ ፋካሊቲ ስር የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ማዕከል (Pedagogical and Educational Research Center/ PERC) በሚል ስያሜ ተመሳሳይ የምርምር ተግባራትን ለማከናዎን ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም በአሁኑ ሰዓት በዩኒቨርሲቲና በአገር አቀፍ ደረጃ የትምህርት ጥራትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ችግር ፈቺ ትምህርታዊ የምርምርና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በተለይም ደረጃቸውን የጠበቁ ታላላቅ የምርምር ፕሮጀክቶችን በመተግበር የሀገሪቱን ዘርፈ-ብዙ የትምህርት ችግሮች ትርጉም ባለው መልኩ ለመቅረፍ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ በትምህርት ፖሊሲ ላይ ተጽእና ማሳረፍ የሚያስችሉ ምርምሮችንና የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶችን እንዲያካሂድ የተመሰረተ ተቋም ነው፡፡

የተቋሙ ራዕይና ተልዕኮ በፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ዘርፍ በሀገራችን ግንባር ቀደምና ተመራጭ የምርምር ተቋም በመሆን ችግርፈቺ ፈቺ ምርምሮችን፣ የማህበረሰብ አገልግሎቶችንና የማማከር ስራዎችን በመስራት ጥራቱንና ተገቢነቱን የጠበቀ ትምህርት በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲና በሀገር ደረጃ ተፈጥሮ ማየት የፔዳጎጂና ትምህርት ምርምር ተቋም ራዕይ ነው፡፡ ይህን ራዕይ ማሳካት ይችል ዘንድ ተቋሙ የሚከተሉትን ተልዕኮዎች በግልጽ በማስቀመጥ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን የትምህርት ጥራት ለማሻሻል የሚያግዙ ምርምሮችን ማካሄድና ምክረሀሳቦችን ለሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው አካላት ማቅረብ፣ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን ስርዓተ ትምህርት ተገቢነትና የመማር ማስተማር ውጤታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ የምርምርና የስልጠና ስራዎችን መስራት፣ በልዩ ልዩ ፔዳጎጂና ትምህርታዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ የምርምር ፕሮጀክቶችን በማካሄድ ለዘርፉ ጠቃሚ የሆኑ አዳዲስ ዕውቀቶችን ማበርከት፣ ተከታታይነት ባለው መልኩ ለትምህርት ባለድርሻ አካላት የተለያዩ የትምህርት ምርምር ውጤቶችን ማቅረብና ማስረጽ፣ በአካባቢው ለሚገኙ የትምህርት ተቋማትና ለተቋማቱ ሙ ያ ተ ኞ ች ( መ ም ህ ራ ን ፣ ርዕሳነመምህራን፣ የትምህርት ኤክስፐርቶችና አመራሮች) የማህበረሰብ አገልግሎትና የማማከር አገልግሎት መስጠት፣ የትምህርት ጥራትን ለማጎልበት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ስልጠናዎችን መስጠት፣ በአካባቢው ማህበረሰብ የትምህርት ልማት እንቅስቃሴዎች በንቃት በመሳተፍ ተቋማዊ ብቃትን ማጎልበት፣ ለተለያዩ የትምህርት ባለድርሻ አካላት በዘርፈ ብዙ የትምህርት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የማማከር አገልግሎት መስጠት፣ ተቋሙን በፋይናንስ ለማጠናከር የሚያግዙ የገቢ ማፈላለግ ስራዎችን ማከናዎን፡፡

የፔዳጎጂና ትምህርት ምርምር ተቋም ማሳካት የሚፈልጋቸውና በፅኑ የሚተገብራቸው ተልዕኮዎች ናቸው፡፡

የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም የተከናወኑ አበረታች ስራዎች

የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም ከተመሠረተበት ከ2005 ዓ.ም ጊዜ ጀምሮ አቅም በፈቀደ መጠን የተጣለበትን ተቋማዊ ኃላፊነት ለመወጣት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በዚህ ረገድ ተቋሙ ካከናዎናቸው አበረታች ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም ለሀገራችን የትምህርት ዘርፍ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለቸው የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ፕሮጀክቶችን ተግብሯል፡፡ ከዩኒቨርሲቲው የሚመደብለትን የምርምር በጀት በመጠቀም በተለያዩ የዩኒቨርሲቲው አካዳሚ ክፍሎች ተመራማሪዎች አማካኝነት ከሀገሪቱ የትምህርት ስርዓት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን የምርምር ፕሮጀክቶች ተግብሯል፡፡ የዩኒቨርሲቲውን የድህረምረቃ ተማሪዎችን በመጠቀም የምርምር ስራዎችን ልምድ በማካፈል እና ምርመሮች እንዲሰሩ የማካሄድ ጥሩ ጅምሬዎች ታይተዋል፡፡

በተመሳሳይ ከአካባቢው ማህበረሰብ ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ተተግብረዋል፡፡በዚህ ረገድ ለሀገሪቱ የትምህርት ዘርፍ ባለድርሻ አካላት በተለይም ለትምህርት ቤት ሙያተኞች (ለመምህራንና ለርዕሳነ መምህራን) የተለያዩ ስልጠናዎችን ማዕከሉ ሰጥቷል፡፡

ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህራን፣ ተመራማሪዎችና የድህረምረቃ ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በዚህ ረገድ በተለያዩ ወቅታዊና ዘመናዊ የትምህርት ጉዳዮች ላይ የህዝብ ገለጻዎችን እና ሴሚናሮችን ማዕከሉ አካሂዷል፡፡ ለመምህራንና ለድህረ ምረቃ ተማሪዎችም በተለያዩ የትምህርት ጥናት አቀራረቦች፣ ዘዴዎችና ቴክኒኮች ለምሳሌ (Advanced Data Analysis Techniques, Qualitative Research, Design Research, Systematic Review) እና የምርምር ሶፍትዌሮች ለምሳሌ (SPSS, MAXQDA, Mendeley Reference Manager) ላይ ጠቃሚ ስልጠናዎችን ሰጥቷል፡፡

ከዚህ ባሻገር በተመረጡ የትምህርት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በርካታ አገርዓቀፍ አውደ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡

ወደ ገጽ 9 የዞረ

## የፔዳጎጂና ትምህርት ------ከገጽ 8 የዞረ

በተመሳሳይ በተቋሙ ሳምንታዊ የአርብሴሚናሮችቁጥራቸውቀላል ያልሆነ ወረቀቶች ቀርበው ሙያው ውይይቶች ተደርጎባቸዋል።

የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም በትምህርትና ስነ-ባሕርይ ሳይንስ ኮሌጅ አዘጋጅነት በሚካሄደው አለምዓቀፍ የትምህርት ምርምር ዓመታዊ የግንቦትጉባዔ (May Conference) በአጋርነት ሲሳተፍ ቆይቷል።

የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም በስራ ሂደቱ ላይ ያጋጠሙት ተግዳሮቶች ምንም እንኳን የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም ከላይ የተጠቀሱትን አበረታች የምርምር ተግባራት ያከናዎነ ቢሆንም ከተቋሙ የሚጠበቁ ሁሉንም ስራዎች በበቂ ሁኔታ መፈጸም አልቻለም ።

ተቋሙ በ10 ዓመታት ጉዞው የተለያዩ ተግዳሮቶች አጋጥመውት ቆይቷል። የበጀት እጥረት የተቋሙ ዋና ተግዳሮት ሲሆን ለአብነት ያህል ባለፉት ሶስት ዓመታት በሀገር ደረጃ ተከስተው በነበሩት በርካታ ችግሮች ሳቢያ ተቋሙ የምርምር በጀት በዩኒቨርሲቲው ባለመመደቡ ለማዕከሉ ከፍተኛ ተግዳሮት በመሆኑ የምርምር ስራዎችን በሙሉ አቅሙ እንዳይሰራ ማዕከሉ የበጀት ጉዳይ እንቅፋት ሆኖበታል።

የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም ተቋሙን በሀላፊነት ከሚመራው ሙያተኛ ውጭ የራሱ ተመራማሪዎች የሉትም። በዚህም የተነሳ ተቋሙ የምርምር ስራወቹን የሚያሰራው ከዩኒቨርሲቲው የተለያዩ አካዳሚ ክፍሎች በሚመረጡ ተጋባዥ ተመራማሪዎች (Research Fellows) አማካኝነት ነው። ይህ ሁኔታ የተቋሙን ራዕይና ተልእኮዎች በበቂ ሁኔታ ከመፈጸም አንጻር ትልቅ ተግዳሮት ሆኖ ይገኛል።

በተቋሙ ተመራማሪዎች ዘንድም በስፋት የሚገለጹ ችግሮች አሉ። ከእነዚህ መካከል የምርምር በጀት በቂ አለመሆን፣ የፋይናንስ ሂደቱ በተመራማሪዎች ላይ የፈጠረው ጫና እና ለተመራማሪዎች በቂ የምርምር ማበረታቻ አለመኖር በዋናነት የሚጠቀሱ የማዕከሉ ተግዳሮቶች ናቸው።

ይህ ብቻም አይደለም በሌላ በኩል በተቋሙ የሚስነዘሩ እጥረቶችም አሉ። ለአብነት ያህል ተመራማሪዎቹ በዩኒቨርሲቲው የፔዳጎጂና የትምህርት ችግሮች ላይ ያተኮሩ ምርምሮችን ለመስራት ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ መሆን፣ የምርምር ፕሮጀክቶችን አሸንፈው በጀት የተፈቀደላቸው ተመራማሪዎች የምርምር ስራቸውን በፕሮፖዛላቸው መሰረት በወቅቱ አለማጠናቀቅ፣ የምርምር ሪፖርቶችን በወቅቱ ገቢ አለማድረግ እንዲሁም የምርምር ግኝቶቻቸውን በዕውቅ የሀገር ውስጥና አለም ዓአቀፍ የምርምር ጆርናሎች የማሳተም ውስንነት ችግሮችም በማዕከሉ በኩል በስፋት ተስተውለዋል።

የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም የታሰበውን ያህል በሀገራዊ የትምህርት ፖሊሲዎች ላይ ተፅእኖ መፍጠር የቻሉ በቂ የምርምር ስራዎችን ሰርቷል ለማለት አያስደፍርም። በተጨማሪም ተቋሙ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን በዓለም አቀፍ ደረጃ እዉቅ የምርምር ዩኒቨርሲቲ የመሆን ራዕይ ከመደገፍ አንጻር ውስንነቶች እንዳሉበት በተለይ በዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮች ዘንድ ሲገለጽ ቆይቷል።

በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ዘንድ በተደጋጋሚ የሚገለፅ ሌላም ችግር አለ። ይኸውም በፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም እና በትምህርትና ስነ-ባህርይ ሳይንስ ኮሌጅ በኩል በሚካሄዱት የምርምር ፕሮጀክቶች መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት እየታየ አይደለም የሚል ነው። በሁለቱ የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች የሚተገበሩት የምርምር ፕሮጀክቶች ትኩረትና ስፋት ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል።

የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም የወደፊት የትኩረት አቅጣጫዎች ቀደም ሲል የተመለከትናቸውን የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም አበራታች ስራዎች አጠናክሮ ለማስቀጠል፣ ተቋሙ የገጠሙትን ተግዳሮቶች ለመፍታት እንዲሁም የተጣሉበትን ተቋማዊ ሀላፊነቶች በአግባቡ ለመፈጸም የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናዎን ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ተቋሙን በተሻለ ሁኔታ መልሶ የማደራጀት ስራ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በአሁን ሰዓት አንድ የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ስራ የገባ ሲሆን ኮሚቴው ተቋሙ ሊመራበት የሚገባውን አደረጃጀትና ስትራቴጂክ እቅድ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል። ይህ ስራ ከተጠናቀቀና የሚመለከታቸውን የዩኒቨርሲቲው አካላት ይሁንታ ካገኘ በኋላ ተቋሙን ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚያስችሉ ተገግባራት የሚከናወኑ ይሆናል። በተለይም ቀደም ሲል የተመለከተውን የተቋሙን ቋሚ የምርምር ሙያተኛ ችግርና የበጀት እጥረት ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችሉ ስራዎች ይሰራሉ።

በቀጣይ ዓመታት የሚፈጠሩትን ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም ተቋሙ የሚከተሉትን ተግባራት በልዩ ትኩረት የሚፈጸም ይሆናል። ምርምር ከፍተኛ በጀት የሚጠይቅ ተግባር በመሆኑና ይህ በጀት በዩኒቨርሲቲው በቂ በሆነ ሁኔታ ሊሸፈን ስለማይችል ተቋሙ በተለያዩ ስልቶች ሀብት የማፈላለግ ስራዎችን የሚሰራ ይሆናል። በዚህ ረገድ ዓለማቀፍ የምርምር ፈንዶችን ተወዳድሮ ማሸነፍና መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ትምህርትነክ የምክር አገልግሎቶችን መስጠት ትልቅ ቦታ ይሰጣቸዋል።

የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ተቋም በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ዘርፈብዙ የትምህርት ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ የምርምርና የስልጠና ስራዎችንም የሚሰራ ይሆናል። በተለይም በዩኒቨርሲቲው ልዩ ልዩ የትምህርት ክፍሎች የሚተገበሩ ስርዓተ ትምህርትቶች ተገቢነትን፣ የመማርማስተማር ሂደትን፣ የመምህራንንየማስተማርናየምዘና ዘዴዎች፣ የትምህርት ግብዓቶች አጠቃቀምና የተማሪ አያያዝን በተመለከተ የምርምር ስራዎችን በመስራት ለሚመለከታቸው አከላት ግብረመልስና ምክረሃሳቦችን የሚሰጥ ትልቅ የምርምር ማዕከል ነው።

መረጃውን ላካፈሉን ለማዕከሉ ዳይሬክተር ለዶ/ር ሙሉጌታ ያየህ በአባይ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ስም እጅግ አድረግን እናመሰግናለን ።

## ዓባይ የቋንቋና የባህል ጥናት ተቋም" ከገጽ 5 የዞረ

በሀገራችን ያለው የፌዴራል የፖለቲካ ስርዓት ለበርካታ ቋንቋዎችና ባህሎች ቀጣይነት አስተዋጽኦ ያበረከተ ቢሆንም፣ አማርኛ ምንም እንኳ በፌደራልም ሆነ በክልሎች እውቅና ከማግኘቱ በዘለለ ቋንቋው የነበረውን እድገት ጠብቆ መቀጠል አልቻለም፤ለዚህም ማሳያ ከሆኑት መካከል አንዱና ዋናው የአምርኛ ቋንቋ ከሀገር አቀፍ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና እንዲወገድ መደረጉ ነው።

በባህል ረገድም ከጥንት ጀምሮ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል፣ በቁስና በድርጊት ሲተላለፉ የነበሩት ፎክሎሮች (ስነ ቃሎች፣ ልማዶች፣ ትውን ጥበባትና ቁሳዊ ባህሎች) በመረሳት እና በመጥፋት እንዲሁም በመጤዎች በመተካት ላይ መሆናቸው ነው።

ባህላዊ እና የክብር አልባሳት፣ ጥንታዊ የብራና ጽሑፎችና የሥነ ሕንፃ ውጤቶች፣ ወዘተ.. በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ አደጋዎች ውድመት እየደረሰባቸው መሆኑ ከፍተኛ ተግዳሮት ነው።

እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቀነስ የተወሰደ የመፍትሔ ሃሳብ ባሕላዊ፣ ታሪካዊ እና አገራዊ ቅርሶች በሳይንሳዊ ዘዴ ሰብስቦ ማጥናት እና በዘመናዊ መንገድ መሰነድ እንዲሁም መቀረስ ተገቢ ስለሆነ ለትምህርትና ለምርምር ሥራዎች ቅድሚያ በመስጠት መስራትና እና ለተጠቃሚዎች ክፍት እንዲሆኑ ማድረጉ እጅግ አስፈላጊ ተግባር ስለሆነ ማዕከሉ በዚህ ዙሪያ በመስራት ላይ ይገኛል።

እንደ ማሳያ የሚሆነውም በአባይ ወንዝ መነሻ በቅርብ ርቀት በሚገኘው በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ "ዐባይ የቋንቋና የባህል ጥናት ተቋም" በሚል ስያሜ አካዳሚያዊ እና ሳይንሳዊ የምርምር ተቋም ማቋቋሙ በጣም አስፈላጊ እና ወቅታዊ መሆኑ ታምኖበት ተቋሙ በ2006 ዓ.ም ወደ ስራ ገብቶ የተለያዩ ተግባራት በማከናዎን ላይ ይገኛል።

# ጤንነት

## Bahir Dar University becomes a member of Consortium of Universities for Global Health



Bahir Dar University becomes a member of Consortium of Universities for Global Health

February 8, 2023, Bahir Dar): Bahir Dar University has become a member of Consortium of Universities for Global Health (CUGH), a Washington, DC, USA, based organization of over 170 universities from around the world that are committed to advancing global health.

CUGH addresses global health issues on behalf of the academic sector and its partners, by helping to harness the capabilities of academic institutions in research, education and service to achieve greater impact. It facilitates knowledge sharing, partnership development and the scaling up of evidence-based solutions to bring new solutions to these challenges. It also promotes and advocates for cooperative interdisciplinary programs in and among member universities.

By being a member of the consortium, the university will be able to get the opportunity for networking with leading academic global health programs and directors, get priority and discounted registration for CUGH's premier annual global health meeting, have strong advocacy voice for academic-based global health programs with government and university leadership, have access to a global health information hub that includes; gain optional program review and evaluation through the Directors' mentorship program; have institutional voting rights in CUGH elections and initiatives, have opportunities for participation in committees/working groups and for institutional representation on the Board of Directors and has access to the CUGH opportunities board.

The university's membership in CUGH will also provide distinct and unique advantages to faculty and students to strengthen and expand their contributions to addressing global health challenges.

It will augment the university's presence in the global health community, facilitate linkages with like-minded academics at institutions around the world, and provide access to information about job, research and training opportunities.

## የተማሪዎች የጤና መረጃ አያያዝ ትግበራ ጀመረ

በወንዳለ ድረስ



የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስፖርት አካዳሚ ከሆፕ ፎር ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር ባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚገኘው ጠይማ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚማሩ ህፃናት የተማሪዎች የጤና መረጃ አያያዝ ትግበራ ጀመረ::

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ ፕሬዝዳንት ተስፋየ ሽፈራው (ዶ/ር) በፕሮጀክቱ ማስጀመሪያ ስነ ስርዓት ላይ ተገኝተው ልጆቻችን ጤናማ ሁነው እንዲያድጉ እና በአዕምሮም በአካልም ብቁ እንዲሆኑ የጤና መረጃ አያያዝ አስፈላጊ ነው ብለዋል፡ ፡ በዚህም ልጆች ከልጅነት ጀምሮ የጤና መረጃ እንዲኖራቸው እና ነገ ችግር ቢያጋጥማቸው አሁን እየለማ ያለው ቴክኖሎጂ እንደ መነሻነት እንደሚያገለግል እና ከምንም በላይ ግን ትምህርት ቤቱ የራሱን አሰራር በማሻሻል ግቢውን ፅዱና ውብ አድርጎ ለጤናማ የትምህርት ስርዓት እንዲስማማ ከማድረግ አንፃር የዩኒቨርሲቲውን ስፖርት አካዳሚ፣ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ የትምህርትና ስነ ባህሪ ኮሌጅ እና የቴክኖሎጅ ተቋማትን ያሳትፋል ብለዋል፡፡ በተማሪዎች የጤና መረጃ አያያዝ ናሙና ትግበራ ማስጀመሪያ የተገኙት የሆፕ ፎር ኢትዮጵያ መስራችና ስራ አስፈፃሚ አቶ ኤርሚያስ ዘውዱ ባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ድርጅቱ የሚያከናውናቸው ተግባራት ንፅህና አጠባበቅ፣ በትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት አቅርቦት፣ ቀጣይነት ያለው የተመጣጠነ የምግብ ፕሮግራም፣ የስፖርት መገልገያዎች እና ቁሳቁሶች ግንባታና አቅርቦት፣ የአትሌቲክስ ስልጠና እና ልማት ፕሮግራሞች እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህር እና ተመራማሪ አለማየሁ ቢሻው/ ፕሮፌሰር/ በበኩላቸው ህፃናት ገና ከጅምሩ በጤናው ዘርፍ ያላቸውን ግንዛቤ በማሳደግ ነገም ሲያድጉ በጤናው መስክ ያላቸውን ሪፖርት በመያዝ በህፃንነታቸው ምን ነበሩ አሁንስ የዚያ ተፅዕኖ ምንድን ነው የሚለውን በማወቅ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ያሉትን ዜጎች በትምህርቱም፣ በጤናውም የተሟላ ስብዕና ተላብሰው እንዲያድጉ ለማድረግ ሆፕ ፎር ኢትዮጵያ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የአራት ሺ ተማሪዎችን የጤና ምዝገባ ለማድረግ በጠይማ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስራውን ጀምሯል ሲሉ ገልፀዋል ፡፡ በዚህም አንድን ዜጋ ለማፍራት በሚደረገው ጥረት የተሳተፉ ተቋማትን አመስግነዋል፡፡ ፕሮግራሙ በዋናነት በትምህርት ላይ ያሉ ህፃናትን የጤና መረጃ በመመዝገብ ከጤና ተቋማት ጋር ማገናኘት ከዚህ ባሻገር ትምህርት ቤት ላይ ያለውን ችግር ለሌሎች ተቋማት በሚደርስ መልኩ በቋሚ መዝገብ እንደሚዘጋጅ የአዲስ አለም ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር እና የህፃናት ሐኪም ስፔሻሊስት ዶ/ር መልካም ደስታ ተናግረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአማራ ባንክ የስትራቴጂ እና ኢኖቬሽን ተጠባባቂ ዋና መኮነን እንዳልሽ ወልደሚካኤል ባንካችን ከባንክ ባሻገር ነው ስንል የባንክ አገልግሎትን በዘመናዊ መንገድ ከመስጠት እና ማህበረሰቡን በስፋት ከማገልገል ባሻገር ለማህበረሰቡ መልሶ በመስጠት የጠነከረ ግንኙነት አለን ብለን እናምናለን፡፡ ይህን ደግሞ የምንገልፅበት በእንደዚህ ያሉ በጎ አገልግሎቶች ነው ብለዋል፡፡

ባህረ- ሀሳብ

# ቆይታ ከመምህርና ተመራማሪ (ዶ/ር) እሸቱ ጋር

## በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ተቋም ውስጥ የሚገኘው ባሕር ዳር ሀይል (Energy) ማዕከል

በባንቹ ታረቀኝ



የባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ከመማር ማስተማሩ ጎን ለጎን በምርምር ስራዎቹ ላይ ለማህበረሰቡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ እና ዩኒቨርሲቲውን የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ አቅዶ እየሰራ ይገኛል። እንዲሁም ወደ 13 የሚጠጉ የምርምር ተቋማት ያሉት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በቴክኖሎጂ ተቋም ውስጥ የሚገኘው ባሕር ዳር ኢነርጂ ማዕከል አንዱ ነው።

ይህ የምርምር ማዕከል ማህበረሰቡን ለማዘመን፣ ችግሮችን ለመፍታት ብሎም ሀገሪቱን ለማሳደግ ከጤና፣ ከግብርና እንዲሁም ከትምህርቱ ጋር በመቀናጀት በቴክኖሎጅው ረገድ አያሌ የሚባሉ የምርምር ስራዎችን በመስራት እና በተግባር ላይ እያዋለ ይገኛል። በዚህ ወር የአባይ ጋዜጣ እትማችን የኢነርጂ ምርምር ማዕከል ዳይሬክተር ከሆኑት ከዶክተር እሸቱ ጌታሁን ጋር ስለ ማዕከሉ ጠቅለል ያለመረጃ ይሰጡናል። መልካም ንባብ…

አባይ፡- ጊዜዎን ሰውተው ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ በመሆንዎ በጋዜጣችን በአባይ ስም ከልብ እናመሰግናለን።
ዶ/ር እሸቱ፡- እኔም አመሰግናለሁ።

አባይ፡- ከስያሜው ብንነሳ የኢነርጂ ምርምር ማዕከል ማለት ምን ማለት ነው?

ዶ/ር እሸቱ፡- ባሕርዳር ኢነርጂ ማዕከል ማለት በዉስጡ የትምህርት እና የምርምር ፕሮግራሞችን የያዘ በኢነርጂው ዘርፍ የሚሰራ የምርምር ተቋም ነው።

አባይ፡- ስለ ባህርዳር ኢነርጂ ማዕከል አጀማመር እንዴት እንደሆነ ቢነግሩን።

ዶ/ር እሸቱ፡- የአንድን ሀገር እድገት ከምንፈልገው ደረጃ ለማድረስ በሁሉም ዘርፍ የሰለጠነ እና ከዘመኑ ጋር የሚራመድ የለውጥ ሀይል ያስፈልጋል። በመሆኑም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአገራችን እድገትና ብልጽግና ለማረጋገጥ የተቀመጡ ግቦችን መሰረት በማድረግ በቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ ትምህርት መስኮች ከፍተኛ ባለሙያዎችን ከማፍራት በተጨማሪ ችግር ፈች ምርምሮችን (የፈጠራ ስራዎችን) በማካሄድና የህብረተሰቡን ህይወት በመሰራታዊነት መቀየር የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የማህበረሰብ አገልገሎቶችን በገጠርና በከተማ በመስጠት የበኩላቸውን ድርሻ በብቃት መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

ስለሆነም ባህር ዳር ኢነርጂ ማዕከል በባህር ዳር ቴክኖሎጂ ኢንስትቲዩት ዉስጥ የሚገኝ ተቋም ሲሆን በአለም አቀፍም ሆነ በሀገር አቀፍ በኢነርጂው ዘርፍ የሚታዩ ችግሮችን ለምፍታት የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመክፈት የበኩሉን አስተዋጻኦ እያበረከተ ይገኛል። ለማህበረሰቡ በበቂ ሁኔታ የሀይል አቅርቦት እንዲዳረስና ለኢንዱስትሪ እድገት ማነቆ የሆነዉን የሃይል አቅርቦት ችግር ለመፍታት ትኩረቱን የአካባቢ ብክለትን የሚቀንሱ የተለያዩ የታዳሽ ሀይል አማራጮች ላይ በማድረግ ስራዉን እየሰራ ይገኛል።

ባህርዳር ኢነርጂ ማዕከል ያሁኑን ስያሜ ያገኘው ከሁለት ፕሮግራሞች ዉህደት ሲሆን የመጀመሪያ ፕሮግራም የትምህርት ክፍል ሲሆን ሁለተኛው ፕሮግራም ደግሞ የምርምር ፕሮግራም ነው። መጀመሪያ የተቋቋመው የትምህርት ፕሮግራሙ ሲሆን የተቋቋመዉም በ 2002 ዓ/ም በዘላቂ ሀይል ምህንድስና በሁለተኛ ድግሪ ፕሮግራም ነው።

በ2003ዓ/ም ይህ የትምህርት ፕሮግራም ወደ የልህቀት ማዕከል በዘላቂ ሀይል አድጓል። የምርምር ማዕከሉ በ2003 ዓ/ም የተቋቋመ ሲሆን ሁለቱም ፕሮግራሞቸ በይበልጥ ስራዎችን በአንድ ላይ ሁነው ለመስራት ያምቾ ዘንድ በ2004ዓ/ም የትምህርት ፕሮግራሙና እና የምርምር ማዕከሉን በአንድ ላይ በማዋሃድ ያሁኑ መጠሪው ባህር ዳር ኢነርጂ ማዕከል ተመሰረተ።

ይህ ማዕከል በ2010 ዓ/ም ተጨማሪ የሶስተኛ ድግሪ ፕሮግራም በዘላቂ ሀይል ምህንድስና በመክፈት ብዙ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።
አባይ፡- የዚህ ማዕከል ራዕይ እና ተልኮ ምንድን ነው?
ዶ/ር እሸቱ፡- የዚህ ማዕከል ራዕይ በኢነርጂ የትምህርት ዘርፍ የፈጠራና የምርምር የልህቀት ማዕከል በመሆን የኢትዮጵያ ኩራት መሆን ሲሆን ተልኮው ደግሞ በተለያዩ የኢነርጂ ቴክኖሎጅ ዘርፎች በእውቀት የታነጹ፣ በክህሎት የዳበሩና በአመለካከት የበሰሉ የቅድመና ድህረ ምረቃ ተመራቂዎችን ማፍራት፣ አገሪቱ ቅድሚያ በምትሰጣቸው ፍላጐቶች በማተኮር ችግር ፈች የኢነርጂ የምርምር ውጤቶችን ማበርከት፣ የቴክኖሎጅ ሽግግርና አካባቢውን መሰረት ባደረገ አገልግሎት በምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት አማካኝነት ለአገራችን የልማት ፍላጐት ምላሽ መስጠት እና በቴክኖሎጅ ፈጠራና በሥራ ፈጠራ የሃብት ፈጠራን ማሳደግ።

ወደ ገጽ 4 የዞረ







## የሳይንስ ጥግ

በባንቹ ታረቀኝ

ይህ አምድ ሳይንስ እና ቴክኖሎጅ ነክ የሆኑ ፅሁፎች ይቀርብበታል

# ባሕር ዳር የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጅነሪንግ እና ሒሳብ ማበልፀጊያ ማዕከል (Bahir Dar STEM INCUBATION CENTER)




ባሕር ዳር የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጅነሪንግ እና ሒሳብ ማበልፀጊያ ማዕከል /Bahir Dar STEM INCUBATION CENTER ስቲም(STEM) የሚለው ምህፃረ ቃል ሲሆን ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና እና ለሂሳብ የትምህርት ዓይነቶች የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡

ይህ ማበልፀጊያ ማዕከል በ2004 ዓ.ም ሲቋቋም በእነዚህ የትምህርት አይነቶችጥሩውጤትለሚያስመዘግቡ ወይም ችሎታ ላላቸው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተማሪዎችን ቁጥር ከፍ ለማድረግ በሚል በሚስተር ማርክ ጌልፋንድ እና በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የገንዘብ ድጋፍ የተደረገ የሁለት ዓመት ፕሮጀክት ነበር፡፡

ይህ ፕሮጀክት "በእያንዳንዱ ልጅ ውስጥ ሳይንቲስትነት አለ" የሚል መርህ ሲኖረው ዓላማው የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ የምህንድስና እና የሒሳብ ተማሪዎችን ቁጥር ማሳደግ ነው፡፡ በዚህ ማበልፀጊያ ማዕከል ተጠቃሚ ለመሆን የሁለቱ መንፈቀ ዓመት የ8ኛ ክፍል ውጤት 85% እና ከዚያ በላይ ያመጡ በማዕከሉ የሚመዘገቡ ሲሆን በመደበኛው የትምህርት ወቅት ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ያጠቃልላል፡፡ በዚህም መሰረት መስፈርቱን አሟልተው ከተመዘገቡ ተማሪዎች ውስጥ በየዓመቱ የትምህርት ቤቱን ፈተና አልፈው ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ 50 ተማሪዎች በማዕከሉ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

በዚህ ማዕከል በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥም 25 ተማሪዎች ሲመደቡ ለእያንዳንዱን ክፍለ ጊዜም አንድ ሰዓት ተመድቦለት ትምህርቱ በዩኒቨርሲቲው መምህራን ይሰጣል፡፡ ይህ ትምህርት ቤት ከሌሎች የሚለየው በማዕከሉ ጥሩ፣ ጥሩ ላበላቶሪዎች ስላሉ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በተግባር እንዲሰሩ ይደረጋል፤ እንዲሁም ከማዕከሉ የሌሉ ላበላቶሪዎችን ወደ ዩኒቨርሲቲዎች በመሄድ ይሰራሉ፡፡

የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርቶች ማለትም ጂኦግራፊ፣ ታሪክ፣ ስነ ዜጋ፣ ስፖርት ሳይንስ እና አማርኛ በሹም አቦ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ት/ቤቶች በሳምንት ሁለት ቀናት ይካሄዳሉ፡፡

ከመደበኛው ፕሮግራም በተጨማሪ በባሕር ዳር ከተማ ከሚገኙ መንግስታዊ እና የግል ትምህርት ቤቶች በክረምት ፕሮግራም ከ5ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች የእድሉ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ በክረምት ለሚማሩ ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲ መምህራን በተጨማሪ፣ የላቦራቶሪ ቴክኒሻኖች፣ የከፍተኛ አንደኛ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት አስተማሪዎች ተመርጠው ተማሪዎችን በቡድን የማስተማር ዘዴን ይጠቀማሉ፡፡ ማለትም ቡድን 1 (5ኛ እና 6ኛ ክፍል)፣ ቡድን 2 (7ኛ እና 8ኛ ክፍል) ቡድን 3 (9ኛ እና 10ኛ ክፍል) እና ቡድን 4 (11ኛ እና 12ኛ ክፍል) ተመድበው እንደ መደበኛው ፕሮግራም እያንዳንዳቸው 25 ተማሪዎች በክፍል ይመደባሉ፡፡

በስልጠናው በዋናነት የሚካተቱ ርዕሰ ጉዳዮች ሳይንስ (ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ ባዮሎጂ)፣ ሒሳብ፣ አይሲቲ፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ ቴክኒካዊ ስዕል/ Technical Drawing/፣ እንግሊዝኛ፣ ፕሮጀክቶች በማንኛውም የትምህርት መስክ ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡

በእያንዳንዱ ክረምት ከ400-500 ተማሪዎች ተጠቃሚ ሲያደርግ ከሀምሌ እስከ ነሃሴ መጨረሻ ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ ከ42-45 ቀናት ወይም 6 ሳምንታት ስልጠና ይወስዳሉ፡፡ ሁሉም በየክረምቱ ለ25 ሰአታት እና በሳምንት 6 ቀናት የሚሰጡ ሲሆን ስልጠናው በሁለት ሽፍት ማለትም ጥዋት እና ከሰአት በኋላም ይሰጣል፡፡ ተማሪዎችን በቤተ ሙከራ ክፍል ውስጥ የሚረዱ ሲሆን የተግባር የላብራቶሪ ሙከራ በማድረግ የተማሪዎችን ገለጻ፣ የሪፖርት አጻጻፍ እና የፕሮጀክት ስራዎችን ይሰራሉ፡፡ ከመደበኛ ትምህርት ውጭም እንቅስቃሴዎች እና የትምህርት ጉዞዎችም በፕሮግራሙ ውስጥ ተካተዋል፡፡

ማዕከሉ በውስጡ የላብራቶሪ ክፍሎች፣ ፊዚክስ፣ የጠፈር ሳይንስ፣ ኬሚስትሪ፣ ባዮሎጂ፣ ባዮኬሚስትሪ፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ ሂሳብ፣ አይሲቲ ፣ አውደ ጥናት፣ ሚኒቤተ መጻሕፍት፣ የመሰብሰቢያ

## ከገጽ 12 የዞረ

አዳራሽ፣ ቢሮዎች፣ የአስተዳዳሪ ክፍል፣ የማከማቻ ክፍል፣ የሰራተኞች ክፍል፣ መጸዳጃ ቤቶች፣ ሰራተኞች (ሴት/ወንድ)፣ ተማሪዎች (ወንድ/ሴት) አሉት፡፡

በማዕከሉ ውስጥ የበጋ ስልጠና፣ የክረምት ስልጠና፣ በአጠቃላይ የትምህርት ዘመን የፕሮጀክት ማማከር እና የአጭር ጊዜ ስልጠና፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ክለቦችን መደገፍ የመሳሰሉት ዋና ዋና ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ከላይ ከተዘረዘሩት የሥልጠና መርሃ ግብሮች በተጨማሪ በባሕር ዳር ዙሪያ የተለያዩ የመዝናኛ ቦታዎችን በትምህርታዊ ጉብኝት ወይም በመዝናኛነት ጉዞዎች ይካሄዳሉ፡፡

ዋና ዋና የጉዞ ቦታዎች የብሉ አባይ ውሃ ፏፏቴ፣ ቆጋ የእርሻ መስኖ ግድብ፣ የባሕር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣ ጎንደር ፋሲለደስ ግንብ እና በሐገሪቱ ውስጥ ያሉትን የሳይንስ ማዕከላት (STEM Centers) ይጠቀሳሉ፡፡

የባሕርዳር የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጅነሪንግ እና ሒሳብ ማበልፀጊያ ማዕከል 12 የእጽዋትና አትክልት ስራ በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጅነሪንግ እና ሒሳብ ማበልፀጊያ ማዕከል የተለመደ ተግባር ነው፡፡

ተማሪዎች በቡድን ሆነው የአትክልት መደቦችን በማዘጋጀት፣ ማዳበሪያ፣ የአፈር ድብልቅ፣ በአቀባዊ የአትክልት መትከል እና የአትክልት ቦታን ውሃ በማጠጣት ይንከባከባሉ፡፡

የአትክልት ስፍራው የመድኃኒት ዕፅዋትን፣ አትክልቶችን እና ሌሎች ለምግብነት የሚውሉ እፅዋትን፣ ፍራፍሬዎችን እና አገር በቀል እፅዋትን መሰብሰብ፣ የአትክልት ስፍራ እና እንዲሁም የባዮጋዝ ማምረቻ ፋብሪካን ያጠቃልላል፡፡

ማበልፀጊያ ማዕከሉ የወደፊት እቅድም አለው፤ ይህም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሙዚየም ማቋቋም፣ የአብነት አዳሪ ትምህርት ቤት መቋቋም፣ በገጠር ላሉ ትምህርት ቤቶች የሞባይል ስቴም ላብራቶሪ መስጠት እና ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የቴሌቪዥን ስርጭት የሚሉት ናቸው፡፡

12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተናማስፈተንከጀመረበትጊዜጀምሮ ሁሉንም ተማሪዎች ለዩኒቨርሲቲ መግቢያ ነጥብ እንዲያስመዘግቡ በማድረግ በሀገር አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኘ ማዕከል ነው፡፡



## ያሰለጠናቸውን በጎፈቃደኛ ወጣቶች አስመረቀ--

## ከገጽ 1 የዞረ





በዛሬው ዕለትም ለ6ኛው ዙር "በጎነት ለአብሮነት" በሚል መሪ ሃሳብ ከ1600 በላይ በጎፈቃደኛ ወጣቶችን ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለአንድ ወር ያሰለጠናቸው በጎ ፈቃደኛ ወጣቶችን በማስመረቅ ወጣቱ ማህበረሰብ እርስ በርስ እንዲተዋወቅ ለማድረግ እና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ተጨማሪ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት አቅም የሚፈጥር መሆኑን ሚኒስቴር ድኤታው ተናግረዋል፡፡ በምራቃ ስነ-ስርዓቱ ላይ ከሰላም ሚኒስትር ለመጡ የስልጠናው አስተባባሪዎች እና ለዕለቱ የክብር እንግዳ ዩኒቨርሲቲው ያዘጋጀውን ሽልማት የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ጉዳዩች ም/ፕሬዚዳንት አቶ ብርሃኑ ገድፍ፣ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው እና የባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ አቶ ባዬ አለባቸው አማካኝነት ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡ የምረቃ ፕሮግራሙን የአማራ ፖሊስ ማርች ባንድና የሙዚቃ ባንድ ዕለቱን አስመልክቶ አጭር ጭውውት፣ ባሕላዊ ሙዚቃዎችን እና ውዝዋዜዎችን በማቅረብ ታዳሚውን አዝናንቷል፡፡ በፕሮግራሙ ላይ በስልጠናው ወቅት የተለያየ ሚና ለነበራቸው የሰላም ሚኒስቴር አመራሮችና አስተባባሪዎች፣ የባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ አመራሮች፣ የአማራ ክልል እና የባህር ዳር ከተማ አስተዳድር ተወካዮች እና የስልጠና አመቻቾች የእውቅና የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል፡፡

## ውድ የዓባይ ጋዜጣ አንባቢያን በዛሬው እትማችን መምህርና ተመራማሪ ዶ/ር ፈነታነሽ ኃይሌን እንግዳ አድርገን ይዘን ቀርበናል መልካም ንባብ

በሙሉጎጃም አንዱዓለም



ውድ አንባቢያን የዚህ ወር እንግዳችን በልጅነት እድሜአቸው ከቤተሰቦቻቸውና ከትዳር አጋራቸው የተፈቀደላቸውን እናትነትና ሚስትነት ካልተፈቀደላቸው ትምህርት ጋር አጣጥመው በርካታ ውጣ ውረዶችን ከውስጣቸው ባለ ወኔ አማካኝነት ታግለው የወጡ፣ 3ኛ ዲግሪአቸውን ከመስራታቸው በፊት የረዳት ፕሮሰሰር ማዕረግ ያገኙና በማህበራዊ ሳይንስ ፋኩልቲም ብቸኛ ሴት ረዳት ፕሮፌሰር የሆኑ ዶ/ር ፈነታነሽ ኃይሌ ከክፍላችን የህዝብ ግንኙነት ባለሙያ ሙሉጎጃም አንዱዓለም ጋር ቆይታ ስላደረጉ ቃለ ምልልሱን እነሆ፦

ዓባይ፡- በቅድሚያ ለቃለ-መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ በዝግጅት ክፍላችን ስም እያመሰገን ስምዎትንና የስራ ኃላፊነትዎን ቢነግሩን?

ፈንታነሽ (ዶ/ር) ፡- እኔም እንግዳ አድርጋቹ ስለጋበዛችሁኝ ክብር ተሰምቶኛል አመሰግናለሁ፤ስሜ ፈንታነሽ ኃይሌ(ዶ/ር) እባላለሁ፣ የመጀመሪያዲግሪዬንከተመረቅኩበት ጊዜ ጀምሮ በባሕር ዳር ዩኒቨርሰቲ በጂኦግራፊ እና አካባቢ ጥናት ት/ት ክፍል በማስተማር ላይ እገኛለሁ

ዓባይ፡- የልጅነት አስተዳደግዎትንና ወደ ትምህርቱ ዓለም እንዴት እንደገቡ ቢያጫውቱን?

ፈንታነሽ (ዶ/ር) ፡- የልጅነት ጊዜዬን በመተከል ዞን ዉስጥ በምትገኝ ድባጢ በምትባል ወረዳ በገጠር ቀበሌ እና በወረዳ ከተማዋ ነዉ ያሳለፍኩት፡፡ ሳድግ ከግብርና ስራዎች አንስቶ ቤተሰብን ሊደጉሙ የሚችሉ እንደ አረቂ ማዉጣት፡ ቦርዲ መጥመቅና መሸጥ የመሳሰሉትን በጥቅሉ ሁሉንም የስራ ዓይነቶች በሚያስብል ደረጃ በመስራት ቤተሰቤን በማገዝ ነዉ ያደግኩት፡፡

ምናልባትም የእኔን አስተዳደግ ልዩ ሊያደርገዉ የሚችል ነገር ቢኖር ቤተሰቤ በኢኮኖሚ ደካማ ከመሆኑ በተጨማሪ አባቴ ብዙ ልጆች እንዲኖሩት የሚወድ ሰዉ በመሆኑና የአካባቢውም ማህበረሰብ ባህል ስለሆነ ከተለያዬ እናቶች ብዙ ልጆችን በመውለዱ ስለ እድገታችን ማሰብ እና መጨነቅ ከእናታችን በተጨማሪ የልጆችም ጭምር ነበር፤ ብንበዛም እህትና ወንድሞቼን እንደምወዳቸዉ መግለጽ እፈልጋለሁ፤ያም ሆኖ ባደግኩበት አካባቢ ማህበረሰብ ለትምህርት ጥሩ አመለካከት በመኖሩ በጊዜ በሚባል እድሜ ላይ ነዉ ት/ት የጀመርኩት፡፡

ዓባይ፡- በ2005 ዓ.ም በናይል ጋዜጣ በወቅቱ በነበሩ አዘጋጆች “በርቾ” በሚል አምድ ላይ ፀሐፊው በቤተሰብ ከተፈቀደ እናትነትና ሚስትነት ጋር ያልተፈቀደውን ትምህርት አጣጥሞ መውጣትን እንዴት እንደቻሉ ስለገለፀው ትምህርትና ሴትነትን እንዴት ያዩታል?

ፈንታነሽ (ዶ/ር) ፡- እንደነገርኩሽ በኢኮኖሚ ደካማ ከሚባል ቤተሰብ ያዉም በርካታ የቤተሰብ ቁጥር ያለን ከመሆኑ በተጨማሪ ከገጠር ከተማ እየተመላለሱ መማር ከባድ ነበር፡፡

በዚህም ምክንያት ትምህርት ማቋረጥ ተመልሶ መግባት አይነት ዉጣ ዉረዶች ነበሩብኝ፡፡ ባልተስተካከለ የኑሮ ጫና ዉስጥ ሆኜም የመማር ፍላጎት እና በተለምዶዉ ሞካሪ ወይም ጎበዝ እሚባል አይነት ተማሪ ስለነበርኩ መምህሮቼ እና የተለያየ ሰዉም በሚሰጠኝ ገንቢ አስተያት ተበረታትቼ ትምህርቴን እየቀጠልኩ ባለሁበት ወቅት በ16 አመቴ የ6ኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ በአንድ መምህር አይን ገባሁና ለትዳር ስጠየቅ ችግርን አሸቀንጥሬ የጣልኩት መስሎኝ ጥያቄውን በደስታ ተቀበልኩ፤

ቤተሰቤም ከእኛ የተሻለ ኑሮ ልትኖሪ ትችያለሽ ብለው በማሰብ “ሙሽሪት ኩሪ ኩሪ ወሰደሽ አስተማሪ” ብለው ዳሩኝ፡፡ ተድሬ ትምህርቴን በመከታተል ላይ እያለሁ 7ኛ ክፍል ላይ የተፈጥሮ ጉዳይ ነውና እርግዝና ተከሰተ ከዛ በኋላ ወደሌላ የህይወት ምዕራፍ ተሸጋገርኩ ትምህርቴንም ለመቀጠል የማልወጣው ተራራ ከፊቴ ተደቅኖ ወደ 8ኛ ክፍል እንዳለፍኩ የበኩር ልጀን ወልጀ የእናትነት ግዴታየን የመወጣት ኃላፊነት ተጠምጀ የኑሮን ውጣ ውረድ ከእለት ወደ ዕለት ሳየው አልዋጥሽ አለኝ፡፡ በዚህ ወቅት የትዳር አጋሬም ሆነ ቤተሰቦቼ ትክክለኛ ቦታዬ ላይ እንዳለሁና ከዚህ የተለዬ ሃሳብ እንዳይኖረኝ ከፍተኛ ጫና ያደርጉብኝ ነበር፡፡

ዓባይ፡-ከሌሎች ሴቶች ጋር የእርስዎን የህይዎት ተሞክሮ ሲያነፃፅሩት እንዴት ይገልፁታል?

ፈንታነሽ (ዶ/ር) ፡- ሰዉ ሁሉ የራሱ የሆነ ፈተና እና እድሎች እንዳሉት ግልጽ ነዉ፡፡ እኔን የገጠሙኝ ፈተናዎች ግን በእኔ እይታ ከባድ ነበሩ ለምሳሌ ያለእድሜ ጋብቻ፣በልጅነት እድሜ መዉለድና የትዳር አጋሬም ወዲያዉኑ ትምህርቴን እንዳቋርጥ ማስገደድ እና የመሳሰሉት ነበሩ፡ ፡ እነዚህን ችግሮች ማሸነፍ ወይም መቀልበስ የሚያስችል ወኔ ከውስጤ ይተናነቀኝ ስለነበር ለሴት ልጅ ሊኖሯት የሚገባ ትዳርና ልጆች ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚ ራሷን መቻል፣

ወደ ገጽ 15 የዞረ

## ከገጽ 14 የቀጠለ

ሃሳቧን መግለጽ፣ተሰሚነቷ መጎልበት ብሎም ዉሳኔ የመስጠትም ሆነ የመቀበል ነፃነት ሊኖራት (ሊኖረኝ) ይገባል የሚል ጽኑ እምነት ስለነበረኝ እና ይህንንም ለማሳካት ለእኔ ብቸኛዉ መፍትሔ ከጨለማ ዉስጥ ፈልጌ ያገኘኋት የብርሃን ጭላንጭል ትምህርቴን ካቆምኩበት መቀጠል እና ዩኒቨርሲቲ መግባት የምትል ቀዳዳ ብቻ አየሁ እሷን ለማስፋት “ወይም ሞት” ብዬ መወሰን ነበረብኝ፡፡

ካለሁበት ማነቆ ለመውጣት መማር ግዴታ መሆኑንና መፈፀሙን ጭምር ለማሳካት ለራሴ ቃል ገብቼ ልጄን እያጠባሁና እየተንከባከብኩ መማር፣ማንበብና ማጥናት ከቤት ስራውጋር ከባድ ቢሆንም ለመፈፀም ቃል ስለገባሁ በአግባቡ የማከናዉን ሰዉ ሆንኩ እግዚአብሔርም ረዳኝና በትምህርቴ ዉጤታማ ሆኜ በመማር ላይ እያለሁ 9ኛ ክፍል ስደርስ ሁለተኛ ልጄን መፀነሴን ባውቅም ብዙ ሳልደናገጥ ራሴን በማጠናከር ትህርቴን ቀጠልኩ፤ወልጀም 10 ቀናት ባልሞላ ጊዜ ወደትምህርት ገበታየ ተቀላቀልኩና በፈጣሪ ቸርነት ጥሩ ውጤት አምጥቼ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪዬን ለመማር ገባሁ፡፡

እኔ መሆን እና መድረስ ለምፈልገዉ ነገር እልህ እና ጥረት አይለዩኝም ነበር፡ ፡ በእርግጠኝነት መናገር የምችለዉ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ለእኔ ያለሁት እኔ ነበርኩ በዚህም ምክንያት ማንም ያበረታታኛል፣ይረዳኛል ብዬ የማልጠብቅ ሰዉ ነበርኩ በአጠቃላይ በሞራልም በዉጤታማነትም በራሴ የምተማመን ሴት ነበርኩ፡፡ሁሌም የሚታየኝ ህልሜን ማሳካት ስለነበረ የምፈልገዉ ቦታ ራሴን አገኘሁት፡፡

ዓባይ፡-ያሁሉ ውጣውረድ አልፎ ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቀው ሲቀጠሩ የተሰማዎትን ስሜት ቢገልፁልን?

ፈንታነሽ (ዶ/ር)፡- በእዉነቱ ያልገመትኩት መልካም አጋጣሚ ነበር ዩኒቨርሲቲዉ የሴት መምህራንን አስተዋፅኦ ማሳደግ አለብኝ ብሎ ከኛ በፊት የነበሩ ተመራቂዎችን እንደቀጠረ ባዉቅም ማስታወቂያዉ እስኪወጣ እርግጠኛ አልነበርንም፡፡ ስንወዳደርም የዉድድር መስፈርቱን አሟሊቼ ስቀጠር በጣም ነዉ ደስ ያለኝ፡፡ እንደነገርኩሽ ለእኔ አይደለም ዩኒቨርሲቲ መቀጠር በዲግሪ ተመርቄ ራሴን መቻል በጣም ትልቅ ስኬት ነበር ዩኒቨርሲቲ ሲሆን ደግሞ አስቢዉ ትልቅ ክብር ስለነበረው ደስታዬ ወሰን አልነበረዉም፡፡

ዓባይ፡-እዚህ ደረጃ ለመድረስ ለዕርስዎ አርያ/ሞዴል/ የሆነዎ ወይም የጥንካሬዎ ምንጭ ምን ይሆን?

ፈንታነሽ (ዶ/ር) ፡- ለእኔ የጥንካሬዬ ምንጭ ያጋጠመኝ ችግር እና ችግሩን መላመድ አለመፈለጌ ነዉ፡፡ ቤተሰቤ ችግሩን እንድላመድና እናት ብቻ ሆኜ እንድኖር ይመክሩኝ ነበር፡፡

በነገራችን ላይ በዚያ ዘመንና በአካባቢው ልማድ ሚስት መደብደብ ፤መገላመጥ፤የእሷን ሃሳብ አለማስተናገድ ትክክለኛ ውሳኔ ወይም በዘመንኛዉ አነጋገር “ኖርማል ነዉ” ተብሎ ስለሚታሰብ እኔም የችግሩ ገፈት ቀማሽ ሆኘ በዚያ ሁኔታ ዉስጥ ነዉ ያለፍኩት፡፡

በነገራችን ላይ በአሁኑ ጊዜም እንደዛ የሚያስቡ ሰዎች አይጠፉም፡፡

ታዲያ ከዚህ ሁኔታ በላይ ምን ሞዴልና አበረታች ነገር ያስፈልጋል ብለሽ ነዉ? ስለዚህ ምን ብየ አስባለሁ መሰለሽ ፈተናዎቼ አሁን ለደረስኩበት ስኬት ጥሩ ስንቆቼ እና ገፊ ምክንያቶቼ ነበሩ፤ካንቺ ጉልበት በላይ የሆነ ጉልበት ወደፊት እየገፋሽ ወደኋላ መመለስ እንደማትችይዉ አይነት ማለት ነዉ፡፡ ወደፊትም ገና ብዙ መስራት እንደሚጠበቅብኝ አምናለሁ፡፡

ዓባይ፡- በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ የዓለም የሴቶች ቀን በተከበረበት መድረክ ላይ ልምድዎን ሲያካፍሉ የነበረው የታዳሚው ድባብ የሚያስገርም ስለሆነ ሌሎች ሴቶች እንደዚህ ጠንክረው እንዲወጡ ምን ይላሉ?

ፈንታነሽ (ዶ/ር) ፡- እኔ ለሴቶች የምመክረዉ ዓላማችንን እንወቅ፣እቅድ ይኑረን፣ለማሳካትም ለራሳችን ቃል እንግባ፣ ለቃላችን ታማኝ እንሁን፣ ካለንበት የተሻለ ነገን መፍጠር እንደምንችልና እንደሚገባን ማመን አለብን ለዚያም የሚመጥን ጥረት፣ጉልበት፣ጊዜ መስጠት አለብን ባይ ነኝ፡፡

ዓባይ፡- በመድረኩ ላይ እርሰዎ 3ኛዲግሪዎን ሲመረቁ በአንድ ቀን ልጅዎም እንደተመረቀች ተነግሯል ስንተኛ ልጀዎ እንደሆነችና በምን ሙያ የት እንደተመረቀች ቢገልፁልን?

ፈንታነሽ (ዶ/ር) ፡- ከእኔ ጋር በአንድ ቀን የተመረቀችው 9ኛ ክፍል እያለሁ የወለድኳት ሁለተኛ ልጄ ናት፤እርሷ በሜዲካል ላቦራቶሪ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ነዉ የተመረቀችው፡፡

ዓባይ፡- በዚሁ አጋጣሚ የቤተሰብዎን ሁኔታ ያሉበትን ደረጃ ጨምረው ቢያጫውቱን?

ፈንታነሽ (ዶ/ር)፡- በአሁኑ ሰዓት የሶስት ልጆች እናት ነኝ፡፡ እኔ በተቻለኝ መጠን ሰላማዊ ህይወት እንዲኖረኝ የምፈልግ እና ያንንም እያስኬድኩ ነዉ ያለሁት፡፡

ዓባይ፡- በአሁኑ ወቅት በልጅነት እድሜዎ የነበረው ጥንካሬ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ የሚያሳይ ተግባር እያከናዎኑ ከሆነ ቢገልፁልን?

ፈንታነሽ (ዶ/ር) ፡- ያዉ ለማስተማር መማር ስላለብኝ እየተማርኩም እያስተማርኩም ነዉ ያለሁት፡፡ ዩኒቨርሲቲዉ ስፖንሰር አድርጎ ካስተማረኝ በተጨማሪ ይጠቅመኛል ያልኩትን ሁለተኛ ዲግሪም በግሌ ተምሬአለሁ፡፡ በተጨማሪም ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎቶች ላይም እሳተፋለሁ፡፡

የምርምር ስራዎችንም እያሳተምኩ እገኛለሁ፡፡ በማሳተሜም የሶስተኛ ዲግሪዬን ከመያዜ በፊት የረዳት ፕሮፌሰርነት ደረጃ ደርሻለሁ፡፡

ከትምህርት ዝግጅት አንጻር (MA in Geography & Environmental , MSc in Geo- Information System, PhD in Environmental Management) ለመማር ችያለሁ፡፡

ዓባይ፡- በመጨረሻም ለሴቶችም ሆነ አጠቃላይ ለአንባቢያን የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለዎትና በእኛ በኩል ቢነሳ ብለው ያሰቡት ነገር ግን ያልተነሳ ጥያቄ ካለ ቢያብራሩልን?

ፈንታነሽ (ዶ/ር)፡- እኔ እነዚያ ሁሉ መከራና ፈተናዎች ያላሸነፉኝ ጠንካራ ሴት ነኝ ብዬ ለእራሴ እዉቅና የምሰጥ፣የማከብርና ለመብቴ የምቆም ሴት ስሆን ደግሞም በጣም ደስተኛ ነኝ፡፡ ምናልባትም ግቢ ዉስጥ ባለኝ እንቅስቃሴ አብዛኛዉ ሰዉ የሚያዉቀኝ በፈገግታና በመግባባት ነዉ፡፡ ለአንባቢያን የምመክረዉ እራሳችንን ለትልቅ ነገር የማጨት ልምድ ይኑረን፣ የተሻለ ነገር ይገባናል ካልን ያን ለማሳካት የሚጠይቀዉን መስዋዕትነት አዉቀን ከሰራንበት እናሳካዋለን፡፡ በትናንሽ ስኬቶች መርካትም ሆነ በትናንሽ ፈተናዎች መዉደቅ/ መሰበር የለብንም፤ህይወታችንን በራሳችን ላይ ሳናካብድ በተገቢው ቦታና ጊዜ ተገቢውን ተግባር የማከናዎን ልምዳችንን እናዳብር እላለሁ፡፡

ዓባይ፡-የስራጊዜዎትን አጣበዉ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከልብ እናመሰግናለን፡፡

ፈንታነሽ (ዶ/ር)፡-እኔም አመሰግናለሁ



የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኳስ ሜዳ

